# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ

# የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

# የፌዴራል አነስተኛ እና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎች ልማት ኤጀንሲ የድጋፍ ማዕቀፎች አፈጻጸምን በተመለከተ የተከናወነ የክትትል ኦዲት ሪፖርት

መጋቢት 2011 ዓ.ም

አዲስ አበባ

# ማውጫ


ማውጫ ........ i

ክፍል አንድ ........ 1

መግቢያ ፤ ........ 1

የኤጀንሲ ዓላማ፣ ሥልጣንና ተግባር፤ ........ 2

ሥልጣንና ተግባር፤ ........ 2

የክትትል ኦዲቱ ዓላማ፤ ........ 5

የክትትል ኦዲቱ ወሰንና ዘዴ፤ ........ 5

የክትትል ኦዲት መመዘኛ መስፈርት፤ ........ 5

ክፍል ሁለት ........ 6

በክትትል ኦዲት ወቅት የተገኙ የኦዲት ግኝቶች፤ ........ 6

የፋይናንስ ብድር አቅርቦት እና አመላለስ አፈጻጸምን በተመለከተ፤ ........ 6

የብድር ዋስትና ፈንድ በተመለከተ፤ ........ 10

የድህረ ብድር ድጋፍና ክትትልን በተመለከተ፤ ........ 12

የማምረቻና የመሸጫ ማዕከላት አቅርቦትን በተመለከተ፤ ........ 15

የማምረቻና የመሸጫ ማዕከላት መሰረተ ልማት የተሟላላቸው መሆኑን በተመለከተ፤ ........ 18

ኢንተርፕራይዞች ደረጃ ዕድገት ሽግግርን በተመለከተ፤ ........ 19

ወደ ማምረቻ፣ መሸጫና የገበያ ማዕከላት የሚገቡ ኢንተርፕራይዞችን በተመለከተ፤ ........ 21

የአነስተኛና ጥቃቅን ኢንተርፕራይዞች የፊትና የኋላ የገበያ ትስስርና ቁርኝት በተመለከተ፤ ........ 24

የማዕከል የቆይታ ጊዜ ጨርሰው ለሚወጡ ኢንተርፕራይዞች ስለሚደረግ ድጋፍ በተመለከተ፤ ........ 26

ለጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት በሚመለከታቸው አካላት መካከል ያለ ቅንጅታዊ አሰራርን በተመለከተ ፤ ........ 27

ክፍል ሦስት ........ 30

የመደምደሚያ ሀሳብ (Conclusion) ........ 30

እርምጃ የተወሰደባቸውና መሻሻል የታየባቸው፤ ........ 30

እርምጃ ያልተወሰደባቸው እና መሻሻል ያልታየባቸው፤ ........ 35

ክፍል አራት ........ 44

የማሻሻያ ሀሳቦች (Recommendation) ........ 44

# ክፍል አንድ

## መግቢያ ፤

1. ማኑፋክቸሪንግ ማለት ማሽንን መሳሪያን ወይም ጉልበትን በመጠቀም ጥሬ እቃ ላይ የቅርጽን፣የመጠን ወይም ይዘት ለውጥ በማድረግ የተሻለ ዋጋ ያለው ምርት ማምረት ማለት ነው፡፡
2. የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎች ሁሉም አስፈላጊ ቢሆኑም የሀገርን ሀብት በመጠቀም ከሚፈጥሩት የሥራ ዕድል፣ ከሚጠቀሙት ቴክኒዎሎጂ፣ ከሚፈልጉት ካፒታል አንጻር ቅድሚያ ትኩረት የሚሰጣቸው ጨርቃጨርቅና አልባሳት፣ ቆዳና የቆዳ ውጤቶች፣ አግሮ ፕሮሰሲንግ፣ ብረታ ብረትና የእንጨት ሥራዎች፣፣ኬሚካል፣ ኮንስትራክሽን ግብዓት፣ ፋርማሲቲካልስ እና ጌጣጌጥ ናቸው፡፡
3. የአነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ልማት ለማፋጠን የሚረዱ የድጋፍ ማዕቀፍ በመቅረጽ ተግባራዊ ማድረግ አስፈላጊ በመሆኑ የደጋፍ ማዕቀፎቹ ተዘጋጅተዋል፡፡ እነሱም፤

<u>የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ልማት አማራጮችን ማመቻቸት፤</u>

- የኢንዱስትሪ ሥራ ፈጣሪነት አስተሳሰብና ክህሎት ልማት፤
- የኢንዱስትሪ መረጃና የምክር አገልግሎት (መዋዕለ ንዋያቸውን የሚያፈሱበት አዋጪ የሥራ ዘርፍ አማራጭ መረጃ የግብዓት፣ የገበያ መረጃ ) መስጠት፤
- የኢንዱስትሪ ኢንቨስትመንትን ለማሳደግ የአዋጭነት ጥናት የንግድ ሥራ ዕቅድ ማዘጋጀት፤
- በካፒታል ሊዝ ፋይናንስ አሰራር ምርትና ጥራትን የሚያሻሽሉ የኢንዱስትሪ ማሽነሪ ማቅረብ፤
- የኢንዱስትሪ ካላስተርና መሰረተ ልማት አቅርቦት፤
- የኢንተርፐርነርሺፕና ቴክኒዎሎጂ ማልማትና ማሻገር፤
- የኢንዱስትሪ ገበያ ልማትና ኢንዱስትሪዎች ትስስር መፍጠር(የገበያ መዳረሻ ማስፋት)
- የኢንዱሰትሪ የጥራት ደረጃና ምርታማነት የማሳደግ አሰራር መፍጠር
- የኢንዱስትሪ የጥሬ ዕቃ ግብዓት አቅርቦት ትስስር መፍጠር ናቸው፡፡ይህንንም ከላይ የተገለጹትን ለማስፈጸም በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር

201/2003 ዓ.ም የማቋቋሚያ ደንብ መሰረት ተቋቁሞ የነበረው የፌዴራል የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ኤጀንሲ ሁለት ቦታ በመከፈል በሚንስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 373/2008 የፌዴራል አነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎች ልማት ኤጀንሲ በሚል ስያሜ በአዲስ መልክ እንዲቋቋም ተደርጓል፡፡

## የኤጀንሲ ዓላማ፤ ሥልጣንና ተግባር፤

4. የኤጅንሲው ዓላማዎች፡-

- በማኑፋክቸሪንግ ዘርፉ ለከፍተኛ ኢንዱስትሪ ልማት ሰፊ መሰረት የሚጥሉ አነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎችን እንዲስፋፉ በማድረግ ፍትሀዊ የሀብት ክፍፍልን ማረጋገጥና ከግብርና መር ኢኮኖሚ ወደ ኢንዱስትሪ መር ኢኮኖሚ የሚደረገውን ሽግግር ማፋጠን ፡፡
- የአነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ልማት ዘርፍ ተወዳዳሪ፤ ቀጣይነት ያለውና ለኢንዱስትሪው ልማት ጠንካራ መሰረት የሚጥል እንዲሆን ድጋፍ የሚሰጡ ተቋማት ማጠናከርና እንዲፈጠሩ መደገፍና ማስተባበር ናቸው፡፡

## ሥልጣንና ተግባር፤

5. ኤጀንሲው የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡፡

- የአነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ልማት ለማፋጠን የሚረዱ ፖሊሲዎችን፤ ስትራቴጂዎችን፤ እቅዶችን፤ፕሮግራሞችን እና ፕሮጀክቶችን ያዘጋጃል፤በመንግሥት ሲፈቀድ ተግባራዊ ያደርጋል፤
- የአነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ልማት ለማፋጠን የሚረዱ የድጋፍ ማዕቀፎች ይቀርጻል ተግባራዊ ያደርጋል፤
- አነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ልማት ምቹ ሁኔታ እንዲፈጠር የሰራል፤ ለተወዳዳሪነታቸው እንቅፋት የሆኑ ጉዳዮችን በጥናት በመለየት መፍትሄ እንዲያገኙ ያደርጋል
- የሀገር ውስጥ ባለሀብቶች በአነስተኛ እና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ እንዲሰማሩ የኢንቨስትመንት ፕሮሞሽን ሥራ ይሰራል፤
- አነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ልማት የሚደግፉና የሚያስተባብሩ የክልል ተቋማትን የማስፈጸም አቅም ይገነባል፤

- የማኑፋክቸሪንገ ዘርፉን የእሴት ሰንሰለት መሰረት በማድረግ ድጋፍ ሰጪ ተቋማት ለአነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ በፍላግትና በእድገት ደረጃ ላይ የተመሰረተ የሥልጠና የፋይናንስ፣ የቴክኖሎጂ ግብዓቶችን ማቅረባቸውን ያረጋግጣል፣
- የአነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ልማትን ሊያፋጥኑና ተወዳዳሪ ሊያደርጉ የሚችሉ የምርጥ ተሞክሮዎችን ጥናት በሀገር ውስጥና በውጪ ሀገር ያካሂዳል፣ ይቀምራል፣ያሰራጫል፣
- የአነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ የዘርፍ ማህበራት እንዲደራጁ አስፈላጊውን ድጋፍ ያደርጋል፣
- የአነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪና ለዘርፉ ልማት ጠቃሚ የሆኑ የአዋጭነት ጥናት እንዲዘጋጅ ያደርጋል፣ መረጃዎችን ይሰበስባል፣ ይተነትናል፣ ያደራጃል፣ ለተጠቃሚዎች ያሰራጫል፣
- ኢንዱስትሪያሊስቶችን ለማጠናከር እና ለመፍጠር የኢንተርፕሪነርሺፕ ፕሮግራም በመቅረጽ ተግባራዊ ያደርጋል የካይዘን የጥራትና ምርታማነት ሥርዓት ተቀናጅቶ እንዲተገበር ያመቻቻል፣ የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን አገልግሎት ያመቻቻል ተግባራዊ ያደርጋል ፣ሞዴል የኢንኪዩቤሽን ማዕከላትን ያቋቁማል እንዲሁም በክልሎች እንዲቋቋሙ ድጋፍ ያደርጋል፣
- በክልሎች ለአነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ አገልግሎት የሚውሉ የኢንዱስትሪ ካላስተር ልማት በማደራጀት መሰረተ ልማት የተሟላላቸው የኢንዱስትሪ መንደሮች እና የገበያ ማዕከላት እንዲገነቡ ተገቢውን እገዛና የአቅም ግንባታ ድጋፍ ያደርጋል፣
- ከአነአስተኛ ወደ መካከለኛ እና ከመካከለኛ ወደ ከፍተኛ ማኑፋክቸሪንገ ኢንዱስትሪ የሚደረገውን ሽግግር ይደግፋል፣ አነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎች እርስ በርስና ከከፍተኛ ኢንዱስትሪዎች ጋር በግብዓት አቅርቦትና በምርት እንዲሁም በቴክኖሎጂ ትስስር እንዲፈጠሩ ያደርጋል ፣የሀገር ውስጥና የውጭ ሀገር የገበያ ትስስር ተጠቃሚ እንዲሆኑ ይደግፋል፣
- ከጥቃቅን ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ወደ አነስተኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ የሚሸጋገሩትን ሥርዓት በመዘርጋት ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በቅንጅት ተግባራዊ ያደርጋል፣

- የአነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ምርታማነትን ለማሳደግ ፣ የሚያመርቷቸው ምርቶች የጥራት ደረጃቸውን የጠበቁ እና ተወዳዳሪ እንዲሆኑ ከዩኑቨርስቲዎች ፣የጥናትና ምርምር ተቋማት፣ከዘርፍ ልማት ኢንስቲቲዩቶች፣ ከቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ተቋማት ከካፒታል ዕቃዎች ሊዝ ከሚያደርጉ ኩባንያዎች እና ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር በሰው ሀብት ልማት፣በጥናትና ምርምር ፣ቴክኖሎጂ ሽግግርና መሰረተልማት በቅንጅት ይሰራል፣ ከእነዚህ ባለድርሻ አካላት ጋር ያለውን ትስስር ያጠናክራል፣ ያስተባብራል፣
- አነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ተወዳዳሪ ለማረግ በጥናት ላይ የተመሰረተ የማበረታቻ፣ የእውቅና እና የሽልማት ሥርዓት እንዲዘረጋ ያደርጋል፣ ተፈጻሚነቱን ያረጋግጣል፣
- በአገር ውስጥና በውጭ አገር አውደርዕይ፣ አውደ ጥናት፣ሴሚናሮችና ተመሳሳይ መድረኮች በማዘጋጀትና በማስተባበር በአነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ የተመሰረቱ ምርቶችና ቴክኒዎሎጂዎች እንዲተዋወቁና ኢንዱስትሪዎች የልምድ ለውውጥ እንዲያደርጉ ከሚመለከታቸው አከላት ጋር በመቀናጀት ሁኔታዎችን ያመቻቻል፣ይደግፋል፣
- የአነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ የአንድ መስኮት አገልግሎት የሚሰጡ ማዕከላትን ያቋቁማል፣እንዲቋቋሙ ድጋፍ ያደርጋል፣
- የአነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ የብቃት ማረጋገጫ ፣ የደረጃና የጥራት ሰርተፊኬሽን እንዲያገኙ ድጋፍ ያደርጋል፣
- በዓለም አቀፍ ደረጃ ብቃቱን ጠብቆ አገልግሎት መስጠት እንዲችል የአነስተኛና መካከለኛ ኢንዱስትሪን ለመደገፍ ተመሳሳይ ዓላማ ካላቸው በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገር ከሚገኙ የግልና የመንግሥት ተቋማት ጋር ትብብር ያደርጋል፣
- ተጠሪነታቸው ለሚኒስቴሩ ከሆኑ ተቋማት ጋር በመተባበር የአነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎች ድጋፍ እንዲያገኙ ያደርጋል፣
- ተመሳሳይ ዓላማ ካለቸው የሀገር ውስጥና የውጭ ሀገር የግልና የመንግስት ተቋማት የሚገኙ ድጋፎችን ያስተባብራል፣
- የንብረት ባለቤት ይሆናል፣ውል ይዋዋላል፣ በስሙ ይከሳል፣ ይከሰሳል፣
- ዓላማውን ከግብ ለማድረስ የሚረዱ ሌሎች ተዛማጅ ተግባራትን ያከናውናል፣

## የክትትል ኦዲቱ ዓላማ፤

6. ቀደም ሲል የፌዴራል የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ኤጀንሲ አሁን የፌዴራል አነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎች ልማት ኤጀንሲ ላይ የድጋፍ ማዕቀፍ አፈጻጸም ላይ በተሰራው ኦዲት ሪፖርት ላይ በተጠቀሱት የኦዲት ግኝቶች እና በተሰጡት የማሻሻያ ሀሳቦች ላይ የተወሰደ የማስተካከያ እርምጃ መኖሩን ለማረጋገጥ ነው፡፡

## የክትትል ኦዲቱ ወሰንና ዘዴ፤

7. የክትትል ኦዲቱ በዋነኛነት የፌዴራል አነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎች ልማት ኤጀንሲ የተከናወነ ሲሆን በተጨማሪም በናሙና በተመረጡ፤ በየካ ክፍለ ከተማ ጥቃቅን እና አነስተኛ ኢንተርፕራይዝ ልማት ጽ/ቤት ፤ በአዲስ ብድርና ቁጠባ ተቋም የየካ ክፍለ ከተማ ቅ/ጽቤት፤የአዲስ አበባ አዲስ ብድርና ቁጠባ ተቋም፤በኦሮሚያ ክልል በሻሸመኔ ከተማ አስተዳደር የሥራ ዕድል ፈጠራና ምግብ ዋስትና ጽ/ቤት፤አቦስቶ የአንድ ማዕከል አገልግሎት መስጫ ጣቢያ፤ የሻሸመኔ ከተማ የኦሮሚያ ብድርና ቁጠባ ተቋም፤

8. ሀዋሳ የኦሞ ማይክሮ ፋይናንስ ምስራቅ ቅ/ጽ/ቤት፤ኦሞ ማይክሮ ፋይናንስ ተቋም የሀዋሳ ከተማ ዲስትሪክት ጽ/ቤት፤የኦሞ ማይክሮ ፋይናንስ ተቋም መናህሪያ ቅ/ጽ/ቤት፤የሀዋሳ ከተማ የሥራ ዕድል ፈጠራና የምግብ ዋስትና ዘርፍ፤ለሚገኙ ለሚመለከታቸው የስራ ኃፊዎች ቃለ መጠይቅ በማቅረብና የድጋፍ ማዕቀፍን በተመለከተ የተዘጋጁ መመሪያዎችን፤ 2007-2010 እቅድና የእቅድ አፈጻም ሪፖርት፤ የካፒታል ዕቃ ሊዝ ፋናንስ ዳይሬክቶሬት የ2010 ሪፖርት፤ማስረጃዎች በመከለስ፤ የተከናወነ ሲሆን፤

9. የክትትል ኦዲቱ ከ2005 ዓ.ም እስከ 2008 ዓ.ም ሩብ ዓመት ድረስ የድጋፍ ማዕቀፍ አፈጻጸምን በተመለከተ በተሰጠው የማሻሻያ ሀሳብ እና ኤጀንሲው ባዘጋጀው የድርጊት መርሃ ግብር መሰረት የተደረጉ የማስተካከያ እርምጃዎች ላይ ትኩረት ያደረገ ነው፡፡

## የክትትል ኦዲት መመዘኛ መስፈርት፤

10. የክትትል ኦዲቱን ለማከናወን እንደመመዘኛ መስፈርት የተመረጡት በኦዲቱ ወቅት የነበሩ የኦዲት ግኝቶችና የተሰጡ የማሻሻያ ሀሳቦች ናቸው፡፡

# ክፍል ሁለት

## በክትትል ኦዲት ወቅት የተገኙ የኦዲት ግኝቶች፣

### የፋይናንስ ብድር አቅርቦት እና አመላለስ አፈጻጸምን በተመለከተ፤

11. ለአነስተኛና ጥቃቅን ኢንተርፕራይዞች የሚደረገውን የፋይናንስና ብድር አቅርቦት ድጋፍ በተመለከተ በስትራቴጂክ ዕቅድ ውስጥ አካቶ በማቀድ በየበጀት ዓመቱ እየተመነዘረ ተግባራዊ መደረግ አለበት፤

12. በቀደመው ኦዲት የፌዴራል ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ኤጀንሲ በየዓመቱ ወደ ሥራ ለሚገቡ ለአዳዲስ ኢንተርፕራይዞች እና ነባር አንቀሳቃሾች የብድር አገልግሎት ለማመቻቸትና እንዲቀርብ ድጋፍ ለማድረግ በስትራቴጂክ ዕቅድ ውስጥ እንዲካተት አድርጓል፡፡ ነገር ግን የብድር ስርጭት ዕቅድ አፈጻጸምን በተመለከተ ከብድር ገንዘብ አቅርቦት አንጻር በዕቅዱ መሰረት ባይከናወንም አፈጻጸሙ በየጊዜው እየተሸሻለ መምጣቱ፤ከብድር ተጠቃሚዎች ብዛት አንጻር ግን አፈጻጸሙ በጣም ዝቅተኛ መሆኑ፣ የብደር መመሪያው የተደራጁ ኢንተርፕራይዞች የንግድ ስራ ዕቅዱን/ የአዋጭነት ጥናቱን ለጽ/ቤት ባቀረቡ በ15 ቀናት ውስጥ ብድሩን እንዲያገኙ ይደረጋል ቢባልም በተጨባጭ ግን በተባለው ጊዜ ውስጥ የማያገኙ መሆኑ፤

13. የተሰጠ ብድር አመላለስን በተመለከተ አበዳሪ ተቋሚት ላይ ወዝፍ ብድር እንዲኖርና ብሔራዊ ባንክ ያስቀመጠውን የ97% የብድር አመላለስ ምጣኔ መመሪያ እንዲሁም ኤጀንሲው ሲያቅድ የተሰራጨውን ብድር 100% መሰብሰብ እንዳለበት በግልጽ ቢያስቀምጥም ነገር ግን በየበጀት ዓመቱ የተሰራጨ ብድርን የማስመለስ አፈጻጸም ሲታይ በ2004 (69%)፣ 2005 (64%)፣ 2006 (75%) እና 2007 ዓ.ም (88%) እንደሆነ፣ የብድር አቅርቦት ከኢንተርፕራይዝ ብዛት ጋር የማይመጣጠን መሆን፤ ኢንተርፕራይዞች የተበደሩትን ብድር በተቀመጠላቸው የቆይታ ጊዜ ከፍለው ባለማጠናቀቃቸው ምክንያት የተጠራቀመ የብድር ውዝፍ እንዲከማች ማድረጉና የሚመለከታቸው የባለድርሻ አካለት ብድር ለመስጠቱ የሚተባበሩትን ያህል ማስመለስ ላይ ትብብራቸው አናሳ መሆኑ፤በኦዲት ግኝቱ ተረጋግጦ ነበር፡፡

14. የፋይናንስና ብድር አቅርቦት በዕቅዱ መሰረት ሊከናወን እና የአነስተኛና ጥቃቅን ኢንተርፕራይዞች የብድር ፍላጎትን ያገናዘበ የብድር አቅርቦት ሊኖር እና ሥራቸው

አዋጪ እስከሆነ ድረስ ብድሩን የሚፈልጉ ኢንተርፕራይዞች ሁሉ ተጠቃሚ የሚሆኑበትን ሁኔታ በማመቻቸት የብድር ተጠቃሚ ኢንተርፕራይዞቹን ቁጥር ከፍ ሊያደርግ እንደሚገባ  የማሻሻያ ሀሳብ ተሰጥቶ ነበር፡፡ ይህንንም ለመተግበር ኤጀንሲው የድርጊት መርሃ ግብር በማዘጋጀት ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ሊልክ ይገባል፡፡

15. ኤጀንሲው በኦዲቱ በተሰጠው የማሻሻያ ሀሳብ መሰረት የእርምት እርምጃ የሚወስድበትን ጊዜ የሚያመላክት የድርጊት መርሃ-ግብር ተዘጋጅቶ ለፌደራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ተልኳል፡፡

16. በክትትል ኦዲቱ ወቅት እንደታየው፤

- ለአዲስና ለነባር የአነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎች የብድር አቅርቦት በሚመለከት ከክልል ለተመለመሉ አስፈፃሚ አካላት የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና እንዲሰጥ መደረጉ፤
- የካፒታል ዕቃ ፋይናንስ ንግድ ስራ አክሲዎን ማህበር ለ1532 ወንድ እና ለ1035 ሴት በድምሩ ለ 2567 የኢንዱስትሪ ባለሀብቶች፣ ሰራተኞች፣ በካፒታል ዕቃ ፋይናንስ ድጋፍ ላይ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና መሰጠቱ፤
- የድጋፍ ማዕቀፍ አፈፃፀም ኦዲት ከየክልሉ ለተመለመሉ አስፈፃሚ አካላት የግንዛቤ ስልጠና እንዲሰጥ መደረጉ፤
- አዲስ ብድርና ቁጠባ ተቋምን በተመለከተ ስለ ወለድ አከፋፈል፣ ስለ አገልገሎት አሰጣጥ ስለ ኢንሹራንስ በቡድንና በማህበር ለተደራጁ በቴክኒክና ሞያ እና የአንድ ማዕከል አገልግሎት መስጫ ጣቢያ ላይ በባለሞያዎች ስልጠና መሰጠቱ፤
- ከአለም ባንክ ከአውሮፓ ኢንቨስትመንት ባንክ በተገኘ ገንዘብ የአነስተኛና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች ፋይናንስ ፕሮጀክት በቅርቡ ስራ የጀመረ ሲሆን በ2011 በጀት ዓመት የመጀመሪያ 6 ወር በተመረጡ ባንኮች ማይክሮ ፋይናንስ ተቋም አማካኝነት በልማት ባንክ በኩል የካፒታል እቃ ተጠቃሚ ለሆኑ 121 ኢንዱስትሪዎች የብር 203.995.000 የስራ ማስኬጃ ብደር እንዲቀርብ መደረጉ፤
- አዲስ ብድርና ቁጠባ ተቋም ኢ.ማ ዋናው መስሪያ ቤት  በዘርፍና በአደረጃጀት በመለየት የመክፈል አቅም ያላቸው የሌላቸው እንዲሁም የጠፉ ኢንተርፕራይዞች በወሰዱት የብድር መጠን ፣ ለምን ያህል ጊዜ እንደቆየ

የሚያሳይ መረጃ በዝርዝር መያዙ፤ብድራቸውን መክፈል ላልቻሉት ሪእስኬጁል እና ሪፋይናንስ በማድረግ ከዚህ በተጨማሪ የእፎይታ ጊዜ በመስጠት ብድራቸውን እንዲከፍሉ መደረጉ፤

- ለአስፈፃሚዎች በተፈጠረው ግንዛቤ ላይ ተመስርቶ በሁሉም ክልሎች በስፋት ወደ ኢንዱስትሪዎች ስለመውረዱ ክትትል በማድረግ ሪፖርት እንዲቀርብ የማይደረግ መሆኑ፤
- የሀዋሳ ከተማ የስራ እድል ፈጠራና የኢንተርፕራይዞች መክፈል ያልቻሉና ውዝፍ ብድር ያለባቸውን ኢንተርፕራይዞች በዘርፍ፤ ባለባቸው የብድር ውዝፍ እዳ እና ለምን ያህል ጊዜ እንደቆየ የሚያሳይ የተዘዋዋሪ ብድር መረጃ ያለ ሲሆን የመደበኛ ብድር መረጃው የሌለ መሆኑ፤
- በ2009 እና በ2010 በጀት ዓመት የካፒታል እቃ ፋይናንስ ተጠቃሚ ከሆኑት ውስጥ የስራ ማስኬጃ ብድር ያገኙትን ኢንተርፕራዞች መረጃ ለብቻው ተለይቶ ያልተያዘ መሆኑ፤የኢንዱስትሪዎች የፋይናንስ ድጋፍ የሚሟላው በሁለት መንገድ ሲሆን በጥሬ ገንዘብ በሚቀርብ ብድር (የስራ ማስኬጃ) እና በአይነት የሚሰጥ የፋይናንስ ድጋፍ (የካፒታል እቃ) ነው በዚህም የካፒታል እቃ ሊዝና ፋይናንስ ዳይሬክተር የ2009 በጀት አመታዊ ዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት ላይ በበጀት አመቱ 5012 ማኑፍክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎች ለስራ ማስኬጃ 5.455.000.000.00 ብድር ለማመቻቸት እቅድ የተያዘ ቢሆንም ብሔራዊ ባንክ የሪፖርት መላኪያ ፎርማቱን ወደ አነስተኛና የብድርና ቁጠባ ተቋም ማውረድ ባለመቻሉ የተሰራጨው የብድር መጠን የማይታወቅ መሆኑ፤
- አዲስ ኢንተርፕራይዝና ነባር አንቀሳቃሾች የስራ ማስኬጃ ብድርን በተመለከተ ስራው በዋነኝነት በክልል ኢንዱስትሪ ቢሮዎች በአበዳሪና በካፒታል ዕቃ ፋይናንስ ተቋማት በቅንጅት የሚሰራ ሲሆን ለአነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎች የስራ ማስኬጃ ብድር መስጠትን በተመለከተ በክልሎች ከቀረበ ሪፖርት በመነሳት በ2009 በጀት ዓመት የተሰጠ የስራ ማስኬጃ ብድር መረጃ ከክልሎች ለኤጀንሲው ሪፖርት ያልቀረበ መሆኑ፤

ኤጀንሲው ;

- በ2009 በጀት አመት ለአነስተኛና መካከለኛ ኢንዱስትሪዎች 7 ቢሊየን ብር የስራ ማስኬጃ ብድር ለማመቻቸት እቅድ ተይዞ 338.743.757.13 ብር የተሰራጨ ሲሆን አፈፃፀሙም 4.8% መሆኑ፤

- በ2010 በጀት አመት ለ8000 አነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎች የብር 6 ቢሊዮን የስራ ማስኬጃ ብድር በአበዳሪ ተቋማት እንዲሰራጭ ክትትል ድጋፍ ለማድረግ ዕቅድ ተይዞ የ3 ክልሎች (ትግራይ፣ ሱማሌ እና ድሬደዋ ) ብቻ ለ817 አነስተኛና መካከለኛ ኢንዱስትሪዎች የሥራ ማስኬጃ ብድር ብር 158.143.568.07 የተሰራጨ ሲሆን፤(የብድር እቅዱን 10.2%) እና በእቅድ ከተያዙት ኢንዱሰትሪዎች ውስጥ ብድር ያገኙት (2.9%) ሲሆን ይህም ከአመታዊ እቅዱ ጋር ሲነፃፀር በጣም ዝቅተኛ መሆኑ፤
- የኢንተርፕራይዞች ልማት ዳይሬክተር የ2010 አመታዊ የአፈፃፀም ሪፖርት ላይ በበጀት አመቱ ለወጣቶች የተሰራጨው ብድር መጠን ኦሮሚያ፤አማራ፤ ደቡብ፤ድሬደዋ፤ጋምቤላ፤አዲስ አበባና ቤንሻንጉል ጉምዝ ክልል ውጭ ሌሎች ክልሎች መረጃውን ለይተው አለመላካቸው
- የካፒታል ዕቃ ሊዝና ፋይናንስ የ2010 በጀት ዓመታዊ ዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት በፌዴራል ደረጃ ለአነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎች የስራ ማስኬጃ ብድር የሚያቀርቡ የፋይናንስ ተቋማት ተለይተው ባለመታወቃቸው በጋራ እቅድ አውጥቶ ለመንቀሳቀስ እንቅፋት መሆኑ፤
- በሻሸመኔ ከተማ የኦሮሚያ ብድርና የአነስተኛ ብድር አቅራቢ ተቋማት ለጥቃቅን አነስተኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንተረፕራይዞች ተደራሽ ስለመሆናቸው የሚያሳይ መረጃ ቢጠየቁም ለአንድ ኢንተርፕራይዝ ብቻ ብድር ያመቻቹ መሆኑ፤
- የካፒታል ዕቃ ፋይናንስ አቅርቦት በተመለከተ ለአነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎች የማምረቻ መሳሪያውን ዋጋ 20 በመቶ እንዲቆጥቡ በማድረግ ቀሪውን የካፒታል ዕቃ ተቋሙ በመሸፈንና መሳሪያውን ገዝቶ በመስጠት ኢንዱስትሪዎቹ እስከ አምስት ዓመት በሚደርስ ጊዜ ክፍያውን የሚፈፅሙበት በአይነት የሚደረግ የፋይናንስ ድጋፍ ሲሆን በዚህም መሰረት በ2009 በጀት አመት ለ2.949 አነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪን ኢንዱስትሪዎች የብር 7 ቢሊየን ማምረቻ መሳሪ እንዲቀርብ ድጋፍ ክትትል ለማድረግ ታቅዶ በበጀት አመቱ 1058 ኢንዱስትሪዎች (የእቅዱን 35.9%) የብር 371.835.094.10 ማምረቻ መሳሪያ (የዕቅዱን 5.3%) የቀረበ መሆኑ፤

- በ2010 በጀት አመት ለ 8354 አነስተኛና መከከለኛ ማኑፍክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎች የብር 8.354.000.000 ማምረቻ መሳሪያ ለማቅረብ ታቅዶ ለ154 አዲስና 779 ነባር በድምሩ ለ933 ኢንዱስቱሪዎች (የእቅዱን 11.17%) እና የብር 720.008.035.16 ማምረቻ መሳሪያ (የእቅዱን 8.6%) የቀረበ መሆኑ አፈፃፀሙ ከእቅድ አኳያ ሲታይ በጣም ዝቅተኛ መሆኑ፤
- ቁጠባን በተመለከተ ይህንን ስራ በዋናነት የሚያከናውኑት ክልሎች ሲሆኑ በሰሩት የግንዛቤ ፈጠራ ስራ ለካፒታል እቃ ፋይናንስ ድጋፍ እንደ ቅድመ ሁኔታ የሚጠየቀው 20 በመቶ ቅድመ ቁጠባ እንዲቆጥቡ በማድረግ ሲሆን የስራ ማስኬጃ ብድር ለማግኘት የተቆጠበውን መረጃ የመሰብሰብ ስራ በኤጀንሲው አለመከናወኑ፤

በክትትል ኦዲቱ ከተከለሱ ማስረጃዎች እና የኤጀንሲው ኃላፊዎች ከሠጡት መልስ ለመረዳት ተችሏል፡፡

**የብድር ዋስትና ፈንድ በተመለከተ፤**

17. የብድር አሰጣጥ አገልግሎት ለማጠናከር እና በመደበኛ ባንኮች የተቀመጡትን የብድር ዋስትና/ማስያዣ (collateral) የማቅረብ አቅም ለሌላቸው ሥራቸውን ለመጀምር ወይም ለማስፋፋት የሚያስችል ብድር እንዲያገኙ ለማድረግ የብድር ዋስትና ፈንድ (Credit guaranteefund) በየክልል መንግስታት/በከተማ አስተዳደሮች መቋቋም አለበት፤ ኢንተርፕራይዞቹም የፈንዱን አላማ ምን እንደሆነ እንዲያውቁት የግንዛቤ ማስጨበጫ በመስጠት ኤጀንሲውም ክልሎች ፈንዱን እንዲያቋቁሙ ተገቢውን ድጋፍ ማድረግ አለበት

18. በቀድሞ ኦዲት ወቅት ከአዲስ አበባ ከተማ መስተዳደር በስተቀር የኦሮሚያ እና የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልሎች የብድር ዋስትና ፈንድ አለማቋቋማቸው፤ በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልል የሐዋሳ ከተማ በኦሮሚያ ክልል በሻሸመኔ ከተማ፣ በታዩ ፋይናንስ አቅራቢ ተቋማት በሰጡት ምላሽና በተሰበሰ መረጃ ለመገንዘብ እንደተቻለው የከተማ መስተዳድሮች በራሳቸው ተነሳሽነት ለኢንተርፕራይዞች የብድር ዋስትና ሽፋን በመስጠት ብድሩ ቢመቻችም፤ ኢንተርፕራይዞች የተበደሩት ገንዘብ በማስመለስ ሂደት ላይ መንግስት ዋስ ሆኖልናል በሚል የተሳሳተ አስተሳሰብ ብድር ማስመለስ አለመቻሉ በኦዲት ግኝቱ ተረጋግጦ ነበር፡፡

19. አነስተኛና ጥቃቅን ኢንተርፕራዞች ሥራቸውን ለመጀመርም ሆነ ለማሻሻል የሚስፈልጋቸውን የፋይናንስ አቅም እንዲያገኙ የሚያግዝ እና ለኢንተርፕራይዞቹ የብድር አሰጣጥ አገልግሎት ለማጠናከር የብድር ዋስትና ፈንድ (Credit guarantee fund) በክልል መንግስታት/ በከተማ አስተዳደሮች ሊቋቋም እነደሚገባ እና በብድር ዋስትና ተጠቅመው የተበደሩ አካላትም የተበደሩትን ገንዘብ በውሉ መሰረት እየከፈሉ መሆኑ ጥብቅ ክትትል የሚደረግበት ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ መደረግ እንዳለበት የማሻሻያ ሀሳብ ተሰጥቶ ነበር፡፡ይህንንም ለመተግበር ኤጀንሲው የድርጊት መርሃ ግብር በማዘጋጀት ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ሊልክ ይገባል፡፡

20. ኤጀንሲው በኦዲቱ በተሰጠው የማሻሻያ ሀሳብ መሰረት የእርምት እርምጃ የሚወስድበትን ጊዜ የሚያመላክት የድርጊት መረሃ-ግብር ተዘጋጅቶ ለፌደራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ተልኳል፡፡

21. በክትትል ኦዲቱ ወቅት እንደታየው

- በድሬደዋ ከተማ አስተዳደር ራሱን ችሎ የተቋቋመ ብድር ዋስትና ፈንድ ባይኖርም ከበጀታቸው ላይ 4.000.000 ለብድር ዋስትና በመመደብ ለድሬ ብድርና ቁጠባ ገቢ ማድረጋቸው ከተማ አስተዳደሩ ለመደበው የብድር ዋስትና በጀት (ብር 4.000.000 ) ረቂቅ የአሰራር መመሪያ መዘጋጀቱ፤
- በሻሸመኔ ከተማ የብድር ዋስትና ፈንድ መመሪያ ተዘጋጅቶ እየተሰራበት መሆኑ፤ በማንዋሉ መሰረት በአፈፃፀም መመሪያው ላይም ስልጠና ለኢንተርፕራይዞች እና ለማዕከል ባለሞያዎች እንዲሰጥ መደረጉ፤
- የኤጀንሲው የድጋፍ ማዕቀፍ አፈፃፀም ኦዲት በቀረበው ሪፖርት ከኤጀንሲው በተጨማሪ ክልል መስተዳድር ፤የከተማ አስተዳደሮች ፤ ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ወዘተ የሚሳተፉበት የድርጊት መርሀ ግብር ያዘጋጀ ቢሆንም እስከ አሁን ድረስ የብድር ዋስትና ፈንድ በየክልሎች እንዲቋቋም አለመደረጉ፤
- የብድር ዋስትና ፈንድ በሁሉም ክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች ስለመቋቋሙ የኤጀንሲው የዘርፍ ምክር ቤት ኃላፊ ተጠይቀው ሲመልሱ የብድር ዋስትና ፈንድ ለማቋቋም መጀመሪያ ኢንዱስትሪዎች ብድር ማግኘት የልቻሉት ዋስትና ማቅረብ ባለመቻላቸው ሁሉም ክልሎች እና ከተማ አስተዳደሮች የብድር ዋስትና ፈንድ የአሰራር መመሪያ አዘጋጅተው ተግባራዊ እንዲያደርጉ ኤጀንሲው ባዘጋጀው የድርጊት መረሃ ግብር ላይ ቢቀመጥም የብድር ዋስትና

ፈንድ ባለመቋቋሙ ምክንያት ክልሎች የአሰራር መመሪያ እንዲያዘጋጁ አለመደረጉን ገልጸዋል፡፡

- በሻሸመኔ፣ ሀዋሳ  የስራ እድል ፈጠራና የምግብ ዋስትና ፅ/ቤት የብድር ዋስትና ፈንድ የአሰራር መመሪያ እንዲዘጋጅ ተደርጓል የተባለ ቢሆንም የአሰራር መመሪያ ሊቀርብ አለመቻሉ፤ በሀዋሳ፤ በሻሸመኔ ስለብድር ዋስትና ፈንድ አሰራር ላይ  ስለፈንዱ (ብድሩ) አጠቃቀም ለቀበሌ አስተዳደር፤ለአንድ ማዕከል ባለሞያዎች እና ለብድርና ቁጠባ ባለሞያዎች ስልጠና እና ግንዛቤ ማስጨበጫ ተሰጥቷል  ቢባልም ነገር ግን መረጃው በማዕከል የማይገኝ መሆኑ፤

በክትትል ኦዲቱ ከተከለሱ ማስረጃዎች እና የኤጀንሲው ኃላፊዎች ከሠጡት መልስ ለመረዳት ተችሏል፡፡

## የድህረ ብድር ድጋፍና ክትትልን በተመለከተ፤

22. ኢንተርፕራይዞች የተበደሩትን ገንዘብ ለታለመለት ዓለማና አቅርበውት በነበረው የሥራ ዕቅድ (Business plan) መሰረት ተግባር ላይ ማዋላቸውን የሚያረጋግጥበት ስርዓት በጥቃቅንና አነስተኛ ልማት ኤጀንሲ መዘርጋት አለበት፡፡

23. በቀድሞ ኦዲት ወቅት  በናሙና በታዩ በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልል የሐዋሳ ከተማ፣ በኦሮሚያ ክልል በሻሸመኔ ከተማ፣ በአዲስ አበባ ከተማ መስተዳደር በታዩ ፋይናንስ አቅራቢ ተቋማት ለመገንዘብ እንደተቻለው የስራቸው ትልቁ ችግር ኢንተርፕራይዞች የተበደሩትን ብድር ለታለመለት ዓላማና አቅርበውት ለነበረው የሥራ ዕቅድ (Business plan) መሰረት ተግባር እንደማያውሉት እና ይህም ስለመሆኑ የሚከታተል ስርዓት በኤጀንሲዎችም (ጽ/ቤቶች) ሆነ በአበዳሪ ተቋማት የተጠናከረ ክትትል የማይደረግ በመሆኑ፤ አንዳንድ ኢንተርፕራይዞች አቅርበውት ከነበረው የሥራ ዕቅድ ውጪ የተበደሩትን ገንዘብ ለሌላ ስራ እያዋሉት መሆኑ በኦዲት ግኝቱ ተረጋግጦ ነበር፡፡

24. በአነስተኛና ጥቃቅን ኢንተርፕርይዝነት ተደራጅተው የብድር ተጠቃሚ ለመሆን የሚያቀርቡት የሥራ ዕቅድ መሰረት የብድር ተጠቃሚ ከሆኑ በኋላ ኢንተርፕራይዞች የተበደሩትን ገንዘብ ለታለመለት ዓላማና አቅርበውት በነበረው የሥራ ዕቅድ (Business plan) መሰረት ተግባር ላይ ማዋላቸውን የሚከታተልበትና

የሚያረጋግጥበት ስርዓት ኤጀንሲው ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን ዘርግቶ ተግባራዊ ማድረግ እንደሚገባ የማሻሻያ ሀሳብ ተሰጥቶ ነበር፡፡ይህንንም ለመተግበር ኤጀንሲው የድርጊት መርሃ ግብር በማዘጋጀት ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ሊልክ ይገባል፡፡

25. ኤጀንሲው በኦዲቱ በተሰጠው የማሻሻያ ሀሳብ መሰረት የእርምት እርምጃ የሚወስድበትን ጊዜ የሚያመላክት የድርጊት መረሃ-ግብር ተዘጋጅቶ ለፌደራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ተልኳል፡፡

26. በክትትል ኦዲቱ ወቅት እንደታየው

- በቢዝነስ ፕላኑ መሰረት ቦታ ማዘጋጀታቸውን የክትትል ፎርማት ተዘጋጅቶ ክትትል መደረጉ፤
- የብድር ገንዘቡም የሚለቀቀው በመጀመሪያ የስራ ማስኬጃ ፤በመቀጠልም የስራው እንቅስቃሴ አዋጭነት ታይቶ ቀሪው እንዲለቀቅ መደረጉ፤
- ብድር ለወሰዱ የአነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎች የቅርብ ክትትልና ድጋፍ ማድረግ የሚያስችል ስርዓት በመዘርጋት ተግባራዊ ማድረግን በተመለከተ ስራው የካፒታል እቃ ፋይናንስ ተቋም እና የብድር አቅራቢ ተቋማት በየደረጃው ካለው የዘርፍ መዋቅር ጋር በቅንጅት የሚሰራ በመሆኑ በኤጀንሲው በቀጥታ የሚሰራ አለመሆኑ፣ ይህም ሆኖ ከ2009 ጀምሮ በየሩብ አመቱ የፋይናንስ አቅርቦትን አስመልክቶ የሚመለከታቸው የክልልና የፌዴራል አስፈፃሚ ባለድርሻ አካላት እንዲገኙ በማድረግ ሪፖርት ቀርቦ ውይይት የሚደረግበት የክትትልና ድጋፍ አሰራር ተግባራዊ በመደረግ ላይ መሆኑ፤
- ብድር ከመሰጠቱ በፊት የሚቀርቡ ቢዝነስ ፕላን አዋጭ መሆኑ እንዲጠና መደረጉን በተመለከተ በካፒታል እቃ ፋይናንስ እና በስራ ማስኬጃ ብድር አቅርቦት አዋጭ ቢዝነስ ፕላንና አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝም የአዋጭነት ጥናት ማቅረብን የሚጠይቅ በመሆኑ ኢንተርፕራይዞች ብድር ለጠየቁት ተቋም እንዲያቀርቡ መደረጉ
- በ2009 በጀት ዓመት ለልማት ባንክና ለካፒታል ዕቃ ፋይናንስ አቅራቢ ተቋምት 3403 ቢዝነስ ፕላን ቀርቦ 2622 የፀደቀ ሲሆን በ2010 በጀት አመት ደግሞ 1971 ቢዝነስ ፕላኖች ቀርበው 1585 ቢዝነስ ፕላኖች የጸደቁ መሆኑ፤ በኢንዱስትሪዎች በኩል የሚቀርቡ ቢዝነስ ፕላኖች ክፍተት ያለባቸው በመሆኑ

ይህንን ለሚደግፍ አስፈፃሚ አካላት በተሻለ ጥራት ያለው ቢዝነስ ፕላን እንዲቀርብ በፌዴራል ደረጃ የአስፈፃሚ አካላትን አቅም ለመገንባት በቢዝነስ ፕላን አዘገጃጀት ላይ ስልጠና መሰጠቱ፤

- በ2010 በጀት ዓመት ለ400 ባለሞያዎች፤ በንግድ ስራ እቅድ አዘገጃጀት ላይ ስልጠና ለመስጠት ታቅዶ ለ795 (199% ስልጠና መሰጠቱ፤በ 2009 በጀት አመት በትግራይ ክልል ለ416 ኢንዱስትሪዎችና ባለሀብቶችና ሰራተኞች በንግድ ዕቅድ አዘገጃጀት ላይ ስልጠና መሰጠቱ ፤ በደቡብ ክልልም በ2009 በጀት ዓመት በ416 እንዲሁም በ2010 በጀት ዓመት በ523 ቢዝነስ ፕላን ዝግጅት ድጋፍ መደረጉ፤
- በሀዋሳ ከተማ የኦሞ ማይክሮ ፋይናንስ ተቋም፤የሃዋሳ ከተማ የስራ እድል ፈጠራና የኢንተርፕራይዞች ብድር ከመሰጠቱ በፊት የሚቀርቡ ቢዝነስ ፕላኖች አዋጭ መሆኑ እንዲጠና ስለመደረጉ የሚያሳይ መረጃ አለመኖሩ፤
- የአዋጭነት ጥናት ኢንተርፕራይዞች ብደር ለጠየቁበት ተቋም እንዲያቀርቡ ቢደረግም መረጃው በካፒታል ዕቃ ፋይናንስና በአበዳር ተቋማቱ የሚሰበሰብና ታይቶ የሚፀድቅ በመሆኑ በኤጀንሲው በኩል የተሟላ መረጃ የመሰብሰብ ስራ አለመሰራቱ፤
- የተሰራጨው ብድር ለታለመለት አላማ መዋሉን 4 ጊዜ ክትትል ለማድረግ የታቀደ ቢሆንም የብድር መረጃውን ማግኘት ባለመቻሉ የብድር ክትትል ስራ ያልተሰራ መሆኑ፤
- የብድር ተጠቃሚ የሆኑ የአነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትዎች ብድር ከወሰዱ በኋላ በተዘጋጀው የንግድ እቅድ መሰረት ለታለመለት አላማ ስለማዋላቸው የቀረበ ማስረጃ የሌለ መሆኑ፤
- በሻሸመኔ ከተማ የኦሮሚያ ብድርና ቁጠባ ተቋም ለሻሸመኔ ቅርንጫፍ ብድር ተጠቃሚ ኢንተርፕራይዞች በተዘጋጀው የንግድ እቅድ ዝግጅት መሰረት ለታለመለት አላማ ስለማዋላቸው ክትትል ስለመደረጉ የሚያሳይ ማስረጃ የሌለ መሆኑ፣
- ኦሞ ማይክሮ ፋይናንስ ተቋም አ.ማ የምስራቅ ቅ/ፅ/ቤት ተጠቃሚ ኢንተርፕራይዞች በተዘጋጀው የንግድ እቅድ ዝግጅት መሰረት ለታለመለት አላማ ስለማዋላቸው ክትትል ስለመደረጉ ማስረጃ አለመቅረቡ፤

- ለኦሞ ማይክሮ ፋይናንስ ተቋም ሃዋሳ ከተማ  የንግድ ስራ እቅድ የአዋጭነት ጥናት የማይጠና መሆኑ ነገር ግን የቀረበውን ቢዝነስ ፕላን የመገምገም ስራ የሚሰራ መሆኑ፣
- ኦሞ ማይክሮ ፋይናንስ ተቋም አ.ማ የምስራቅ ቅ/ፅ/ቤት  ብድር ከመሰጠቱ በፊት የሚቀርበው ቢዝነስ ፕላን አዋጭ መሆኑ እንዲጠና ስለመደረጉ የሚያሳይ ማስረጃ የሌለ መሆኑ፣

በክትትል ኦዲቱ ከተከለሱ ማስረጃዎች እና የኤጀንሲው ኃላፊዎች ከሠጡት መልስ ለመረዳት ተችሏል፤

## የማምረቻና የመሸጫ ማዕከላት አቅርቦትን በተመለከተ፤

27. ኤጀንሲው ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመቀናጀት የማምረቻና የመሸጫ ማዕከላት የስትራቴጂክ ዕቅድ በማውጣት በየዓመቱ በመመንዘር እየገነባ ለኢንተርፕራይዞቹ ማቅረብ አለበት፣

28. በቀድሞ ኦዲት ወቅት በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልል የሐዋሳ ከተማ በኦሮሚያ ክልል በሻሸመኔ ከተማ፣ በአዲስ አበባ ከተማ መስተዳደር በታዩ ማዕከላት ግንባታቸው ተጠናቀው ሁለት ዓመት ቢያስቆጥርም ለኢንተርፕራይዞቹ እንዳልተላለፉ ከመስክ ጉብኝት ለመገንዘብ ተችሏል፡፡

29. ይህን በተመለከተ የኤጀንሲው ኃላፊዎች በቀረበላቸው መጠይቅና በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ በሰጡት ምላሽ በ5 ዓመታት ውስጥ ለመገንባት ከታቀዱት የሼድ፤ የህንፃና የማምረቻ ቦታ አቅርቦት ሙሉ በሙሉ መሳካቱንና መሰረተ ልማት  ሳይሟላላቸው ለብዙ ጊዜ የተቀመጡ የማምረቻና የመሸጫ ህንጻዎች እንዳሉ  ኤጀንሲው የሚያውቅ መሆኑ በኦዲት ግኝቱ ተረጋግጦ ነበር፡፡

30. የማምረቻና የመሸጫ ማዕከላት እና ሼዶች ግንባታ ለማካሄድ የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላትን ባሳተፈ ሁኔታ የሚገነቡት ማዕከላት ብዛት በጥናት ላይ ተመስርቶ ሊታቀድ እንደሚገባ የማሻሻያ ሀሳብ ተሰጥቶ ነበር፡፡ ይህንንም ለመተግበር ኤጀንሲው የድርጊት መርሃ ግብር በማዘጋጀት ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ሊልክ ይገባል፡፡

31. ኤጀንሲው በኦዲቱ በተሰጠው የማሻሻያ ሀሳብ መሰረት የእርምት እርምጃ የሚወስድበትን ጊዜ የሚያመላክት የድርጊት መረሃ-ግብር ተዘጋጅቶ ለፌደራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ተልኳል፡፡

32. በክትትል ኦዲቱ ወቅት እንደታየው

- አለም አቀፍ ደረጃውን የጠበቀ የክላስተር ማዕከላት ዲዛይን በሞዴልነት ለማባዛት ቀደም ሲል የማስተር ፕላኑና የአርክቴክቸራል ዲዛይን ስራውን በሠራው የምህንድስና አማካሪ ድርጅት ለሁሉም ክልሎች እና ከተማ አስተዳደሮች የሚሆን የNational Prototype Design በማሰራትና ክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች ኮርፖሬሽኖች Adapte አድርገው እንዲጠቀሙበት ዲዛይኖቹ እንዲደርሳቸው መደረጉ፣
- ክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች ለማምረቻ ክላስተሮች ግንባታ የሚውል መሬት በእስታንዳርዱ መሰረት እንዲዘጋጅ ማድረጋቸው፤
- በሀረሪ ክልል መሬት ዝግጅትን በተመለከተ በክልል ደረጃ መዘጋጀት ከሚገባው ባለ 100 እና ባለ 250 ሄክታር ውስጥ ባለ 50 ሄክታር መሬት መዘጋጀቱ፣
- በሻሸመኔ በከተማ አስተዳደሩ በኩል የሚመለከታቸው የኮንስትራክሽን ቢሮ ፣ የከተማ ልማት ቢሮ ፣ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ በጋራ በመሆን ክትትልና ድጋፍ መደረጉ፣
- የመሰረተ ልማትና ክላስተር ዳይሬክተር የአፈፃፀም ሪፖርት መሰረት በነባርና በአዲስ መልክ ሊገነቡ በታሰቡ የክላስተር ማዕከላትና በክላስተር አስተዳደር ስራዎች አዳዲስ አሰራሮች ዙሪያ የአቅም ግንባታ ለ180 አመራሮችና ባለሞያዎች 2 ጊዜ የውይይት መድረክ በማዘጋጀት የጋራ ግንዛቤ እንዲፈጠር ለማድረግ አቅድ የተያዘ ቢሆንም ስራው አለመሰራቱ፣
- በአማራ 6188 ሄክታር፣ በትግራይ 3474 ሄክታር፣ በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች 3068 ሄክታር እና በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር 100 ሄክታር የተዘጋጀ ሲሆን የፕሮቶ ታይፕ ዲዛይንም በፌዴራል ደረጃ ተዘጋጅቶ ለክልሎች እንዲደርስ የተደረገ ቢሆንም ክልሎች የግንባታ በጀት መድበው ወደ ስራ ያልገቡ መሆኑ፣
- በአማራ ክልል በተለያዩ ከተሞች የመሬት ዝግጅት በማድረግ 6234.85 ሄክታር መሬት ቢዘጋጅም ካሳ ተከፍሎበት ከሶስተኛ ወገን ነጻ የተደረገ መሬት መጠን በድምሩ ሲታይ 82.1 ሄክታር ብቻ መሆኑ፣
- በትግራይ ክልል 3473.85 ሄክታር መሬት ለክላስተር ልማት ቢዘጋጅም ካሳ ተከፍሎ ከሶስተኛ ወገን ነፃ የሆነው 384.98 ሄክታር መሬት ብቻ መሆኑ፣

- የ2010 በጀት አመት የዝግጅት ምዕራፍ የአዲስ አበባ እና የኦሮሚያ የክልል የተደረገ የክትትልና ድጋፍ ሪፖርት እንደተመለከተው የምህንድስና የRTS ጥናቶች ተጨባጭ የመሬቱን ዳታ (መረጃ) ሳይወስዱ ዝም ብለው የአካባቢውን ህብረተሰብ በቃል ጠይቀው ባገኙት መረጃ መሰረት ተደርጎ በመሰራቱ ምክንያት በአንድ አከባቢ መሆን ያሌለባቸው ምርቶች በአንድ ቦታ እንዲመረቱ መደረጉ፣
- ለኤክስፖርት ሊሆኑ የሚገባቸውን ምርቶችን ለማምረት አለመቻሉ፤
- በኦሮሚያ ክልል ቡልቡላ ከተማ ላይ የተሰራው ስትራክቸራል ዲዛይን የንፋስ አቅጣጫው የተሳሳተ መሆኑ፣ በተጨማሪም ፎቶ ብቻ ካልሆነ በስተቀር ተጨባጭ ነገሮችን የሚያሳይና ያገናዘበ አለመሆኑ፡ ውሃ የሚወጣበትን ቦታ በድጋሚ በኦሮሚያ ውሃ ሥራዎች ኢንተርፕራይዝ እያስጠኑ መሆኑ፤
- በጋምቤላና በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች ክልላዊ መንግስት ክልል በተደረገ ድጋፍና ክትትል ሪፖርት እንደተመለከተው፤
- በጋምቤላ ከተማ ለኢንዱስትሪ ክላስተር ማዕከል ግንባታ 250 ሄክታር መዘጋጀት ሲኖርበት 100 ሄክታር ብቻ መዘጋጀቱ እንዲሁም በ13 ወረዳዎች እና በ1 ልዩ ወረዳ መዘጋጀት ያለበት 50 ሄክታር መሬት ያለመዘጋጀቱ፣
- በሶማሌ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ፤በሀረሪ ህዝቦች ክልላዊ መንግስት እና የድሬደዋ ከተማ አስተዳደር የ2010 መጀመሪያ ዙር የድጋፍና ክትትል ሪፖርት እንደተመለከተው በሶማሌ ክልል ለክላስተር ማዕከላት መዘጋጀት የሚገባው ባለ 50 ፤ባለ 100 እና ባለ 250 ሄክታር መሬት ያልተዘጋጀ መሆኑና ከ 3ኛ ወገን ነፃ አለመደረጉን፣ ለማስጀምር ያክል እንኳን ከክልሉም ሆነ SDG በጀት አለመመደቡን ለመረዳት ተችሏል፡፡
- የ2009 የመሰረተ ልማትና ክላስተር ዳይሬክተር የአፈፃፀም ሪፖርት ላይ እንደተመለከተው በሞዴልነት የክላስተር ማዕከላት ፕላን ለሌሎች ክልሎችና ከተሞች አገልግሎት እንዲውሉ ከሚለሙ እና ከሚለዩ መሬቶች ጋር የማጣጣም ስራ እንዲሰራ ክትትል የማድረግ ስራ በእቅድ የተያዘ ቢሆንም ያልተሰራ መሆኑ፤
- በክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች የተዘጋጀውን ክላስተር ማዕከላት ልማት ፕላን በተመረጡ ከተሞች መተግበር እንዲችሉ ክትትልና ድጋፍ የማድረግ ስራ በእቅዱ መሰረት ያልተሰራ መሆኑ፣

- በክትትል ኦዲቱ ከተከለሱ ማስረጃዎች እና የኤጀንሲው ኃላፊዎች ከሠጡት መልስ ለመረዳት ተችሏል፡፡

**የማምረቻና የመሸጫ ማዕከላት መሰረተ ልማት የተሟላላቸው መሆኑን በተመለከተ፤**

33. ለጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች የማምረቻና የመሸጫ ማዕከላት የከተሞችን ፕላን መሰረት በማድረግ በአገር አቀፍ ደረጃ በተዘጋጀው ስታንዳርድ ዲዛይን መሰረት በየማዕከላቱ ውስጥ አስፈላጊ የሆኑ መሰረተ ልማት (መንገድ፣ መብራት፣ ውሃ፣ ሥልክ፣) ደረቅ ቆሻሻ ማጠራቀሚያ፣ የጥበቃ ቤት አሟልተው እንዲገነቡ መደረግ አለበት፤

34. በቀድሞ ኦዲት ወቅት በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልል የሐዋሳ ከተማ፣ በኦሮሚያ ክልል በሻሸመኔ ከተማ፣ በአዲስ አበባ ከተማ መስተዳደር ለመገንዘብ እንደተቻለው ከ2004 እስከ 2007 ዓ.ም ውስጥ ኤጀንሲው ተገንብተው ለማስተላለፍ ካቀደው የማምረቻና የመሸጫ ማዕከላት ውስጥ የሕንጻ ግንባታቸው ተጠናቆ ልዩ ልዩ መሰረተ ልማቶች (መንገድ፣ መብራት፣ ውሃ፣ ሥልክ)፣ደረቅ ቆሻሻ ማጠራቀሚያ፣ የጥበቃ ቤት ባለመሟላቱ ለኢንተርፕራይዞቹ ያልተላለፉ መኖራቸውን፣ ለኢንተርፕራይዞቹ ተላልፈው ሥራ የተጀመረባቸው ማዕከላትም ቢሆኑ መሰረተ ልማቶቹ ሳይሟላላቸው እንደተላለፈላቸውና በዚህም ምክንያት እንደተቸገሩ በተጨማሪም በአዲስ አበባ ከተማ መስተዳደር የተገነቡ የማምረቻና የመሸጫ ማዕከላት የግንባታ ጥራት ችግር ያለባቸው መሆኑን በኦዲት ግኝቱ ተረጋግጦ ነበር፡፡

35. የማምረቻና የመሸጫ ማዕከላት እና ሼዶች ግንባታ ለማካሄድ የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላትን ባሳተፈ ሁኔታ የሚገነቡት ማዕከላት ብዛት በጥናት ላይ ተመስርቶ ሊታቀድ ይገባል፡፡ የሚገነቡትም ማዕከላት እና ሼዶች በአገር አቀፍ ደረጃ በተዘጋጀው ስታንዳርድ ዲዛይን መሰረት በማድረግ እና የየከተሞቹን ፕላን ከግንዛቤ ውስጥ በማስገባት መገንባት አለባቸው፡፡ ከማዕከላቱ ግንባታ ጋር አብረው መሟላት የሚገባቸው የመሰረተ ልማቶች (መንገድ፣ መብራት፣ ውሃ፣ ሥልክ)፣ ደረቅ ቆሻሻ ማጠራቀሚያ፣ የመጸዳጃ ቤት፣ የጥበቃ ቤት የመሳሰሉት ተሟልተው ሊገነቡ እንደሚገባ የማሻሻያ ሀሳብ ተሰጥቶ ነበር፤ ይህንንም ለመተግበር ኤጀንሲው የድርጊት መርሃ ግብር በማዘጋጀት ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ሊልክ ይገባል፡፡

36. ኤጀንሲው በኦዲቱ በተሰጠው የማሻሻያ ሀሳብ መሰረት የእርምት እርምጃ የሚወስድበትን ጊዜ የሚያመላክት የድርጊት መረሃ-ግብር ተዘጋጅቶ ለፌደራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ተልኳል

37. በክትትል ኦዲቱ ወቅት እንደታየው፣

- ለነባር የማምረቻ ማዕከላት የመሠረተ ልማት ለማሟላት የመረጃ ችግሮች ቢኖሩም መረጃን በተገኘው አጋጣሚ በማሰባሰብ ከባለድርሻ ተቋማት ጋር የሚሰራው ሥራ የመሥራት ውስንነት ቢኖረውም እንዲቀጥል መደረጉ፣
- የምርት ማሳያና መሸጫ ስታንዳርድ ዲዛይን ለማዘጋጀት በተያዘው እቅድ ላይ ዋናው ስራ የሚካሄድበት በጀት ከአጋር የልማት ድርጅቶች የሚገኝ ቢሆንም የምህድስና አማካሪ ድርጅቶችን ፍላጎት ለማወቅ የተዘጋጀውን የጨረታ ሰነድ እንዲደርሳቸው በኤጀንሲው በኩል ተግባራዊ ማድረግ አለመቻሉ፣
- የ2009 የመሰረተ ልማትና ክላስተር ዳይሬክተር የአፈፃፀም ሪፖርት ላይ እንደተመለከተው በክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች በአዲስ መልክ በተዘጋጀው የክላስተር ማዕከላት ፕላን መሰረት ትኩረት በተሰጠባቸው ዘርፎች ለማምረቻነት የሚውሉ 106 ህንፃዎችን በስታንዳርድ ዲዛይን እንዲገነቡ ድጋፍ ለማድረግ እቅድ የተያዘ ቢሆንም ስራው ያልተሰራ መሆኑ፣
- በማዕከላት እንዲሁም በኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት ኮርፖሬሽን አደረጃጀት መጠናቀቅ ባለመቻሉ ነባር የክላስተር ማዕከላት ተረክቦ ተገቢውን መሰረተ ልማት በመሟላት ለኢንዱስትሪያሊስቶች ማሸጋገር ያልተቻለ መሆኑ፤
- በክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች በተላከላቸው የመረጃ ማሰባሰቢያ ፎርማት መሰረት የተሰበሰበው መረጃ እንደሚያሳየው ለማምረቻና ለመሸጫ ታስበው የተገነቡ ህንፃዎች 968 ሲሆኑ ከነዚህ ውስጥ 278 ህንፃዎች መሰረተ ልማት ያልተሟላላቸውና ለአነስተኛና መካከለኛ ኢንዱስትሪዎች አገልግሎት የማይሰጡ መሆናቸው

በክትትል ኦዲቱ ከተከለሱ ማስረጃዎች እና የኤጀንሲው ኃላፊዎች ከሠጡት መልስ ለመረዳት ተችሏል፡፡

### ኢንተርፕራይዞች ደረጃ ዕድገት ሽግግርን በተመለከተ፤

38. አነስተኛ እና ጥቃቅን ኢንተርፕራይዞች ወደ መካከለኛ ኢንዱስትሪ የሚያድጉበት ሁኔታ መመቻቸት አለበት፡፡ ኤጀንሲው የኢንተርፕራይዝ ደረጃ ሽግግር ከማድረጉ

በፊት በየዕድገት ደረጃው በዓይነት፣ በቁጥርና በዘርፉ ብዛታቸውን ለይቶ መረጃውን ሊይዝና በዚህም መሰረት በየአመቱ ወደ መካከለኛ ኢንተርፕራዝነት የሚሸጋገሩትን መጠን በማቀድ ተግባራዊ መደረግ አለበት፤የሽግግሩን ዕቅድ በተመለከተም በየደረጃው ለሚገኙ አስፈጻሚ አካላት ለተግባራዊነቱ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሊሰጣቸውና ተገቢውን ድርሻ እንዲወጡ መደረግ አለበት፤

39. በቀድሞ ኦዲቱ ወቅት ኤጀንሲው በሀገር አቀፍ ደረጃ ካሉት ኢንተርፕራይዞች በየዓመቱ ከ1-2% ወደ መካከለኛ ባለሀብትነት ለመሸጋገር ግብ የጣለ ቢሆንም በየደረጃው ያሉት ኢንተርፕራይዞች የእያንዳንዱ ብዛት ስንት እንደነበረ በግቡ ላይ በቁጥር ባለመጠቀሱ ዕቅዱ መሳካቱን ማረጋገጥ አልተቻለም፡፡ በናሙና በታዩት በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልል የሐዋሳ ከተማ በኦሮሚያ ክልል በሻሸመኔ ከተማ፣ በአዲስ አበባ ከተማ መስተዳደር በታዩ ከተከለሱ ዶክመንቶች በተገኘ መረጃ መሰረት ወደ ቀጣይ የዕድገት ደረጃዎች ለማሸጋገር የማሸጋገሪያ ስትራቴጂውን ያለመረዳትና የተረዱትንም ስራ ላይ ለመዋል እንደተቸገሩ በኦዲት ግኝቱ ተረጋግጦ ነበር፡፡

40. ኤጀንሲው በአገሪቱ ውስጥ ያሉትን የአነስተኛና ጥቃቅን ኢንተርፕራይዞች ዝርዝር መረጃ በየዕድገት ደረጃው በዓይነት፤ በቁጥርና በዘርፉ ብዛታቸው ለይቶ ዘመናዊ መረጃ አያያዝ ዘዴን በመጠቀም በተጠናከረ ሁኔታ ሊይዝ እንደሚገባ የማሻሻያ ሀሳብ ተሰጥቶ ነበር፡፡ ይህንንም ለመተግበር ኤጀንሲው የድርጊት መርሃ ግብር በማዘጋጀት ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ሊልክ ይገባል፡፡

41. ኤጀንሲው በኦዲቱ በተሰጠው የማሻሻያ ሀሳብ መሰረት የእርምት እርምጃ የሚወስድበትን ጊዜ የሚያመላክት የድርጊት መረሃ-ግብር ተዘጋጅቶ ለፌደራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ተልኳል፡፡

42. በክትትል ኦዲቱ ወቅት እንደታየው፤

- የአነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎች ዝርዝር መረጃ በአገር አቀፍ ደረጃ ወጥ በሆነ መልኩ ለመሰብሰብ እንዲቻል ቅፅና ማንዋል በኤጀንሲው ተዘጋጅቶ ለየክልሉ መላኩ፤ ከክልል ለመጡ ኃላፊዎች እና ባለሞያዎች በመረጃ አሰባሰብ፤አያያዝና አደረጃጀት ላይ ስልጠና መሰጠቱ፤
- ታዳጊ መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎች ማዕከላት የገቡ ኢንዱስትሪዎች መረጃ በአግባቡ በማደራጀት እንዲያዝ መደረጉን በተመለከተ ወደ ማምረቻ ማዕከላት የገቡ ኢንዱስትሪዎችን መረጃ በማደራጀት ረገድ

በነባር ማምረቻ ማዕከላት የክልሎች ወጥ የሆነ የአሰራር የባለቤትነት ችግር በመኖሩ መረጃውን በአግባቡ ማደራጀት አለመቻሉ፣

- የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቢሮ የካ ፤ኮልፌ እና አቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተሞች በራሳቸው ቅፅ የሚጠቀሙ መሆኑን ለማረጋገጥ መቻሉ፤
- በጋምቤላ ክልል የአነስተኛ እና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎች ቆጠራ አለመደረጉ እና ከስራ እድል ፈጠራና ምግብ ዋስት ኤጀንሲ ወደ አነስተኛ እና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎች ልማት ኤጀንሲ አለመተላለፋቸው፤
- ክልሎች የላኩት መረጃ በሚፈለገው ደረጃ ጥራቱን ያልጠበቀና ያልተሟላ በመሆኑ በኦሮሚያ፤ በትግራይ፤በደቡብና ፤በአማራ ፤በሀረሪ ፤በአዲስ አበባ እንዲሁም በድሬደዋ ከተማ አስተዳደር የ2010 በጀት ዓመት የዝግጅት ምዕራፍ የድጋፍ ክትትል ስራ የተጠቃለለ ሪፖርት ላይ ዝርዝር የኢንተፕራይዞች መረጃ መሰብሰብያ ቅፅን በተሟላ ሁኔታ እየተጠቀሙበት አለመሆኑ ፤
- በተለያዩ ቅፆች መረጃዎችን ለማሰባሰብ ጥረት እየተደረገ ቢሆንም በተዘጋጀው ወጥነት ባለው የመረጃ ማሰባሰቢያ ፎርማት መሰረት መረጃ የማይሰበሰብ መሆኑ፤
- በአፋርና በቤንሻንጉል ጉምዝ ክልል ከጥቅምት 6-13 /2010 በተደረገ ክትትልና ድጋፍ በክልሉ የሚገኙ አነስተኛ እና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎች የመለየት ስራ በአሶሳ ከተማ ብቻ ያሉት እንደተለዩና በሌሎች ዞኖች የሚገኙት ያልተለዩ መሆኑ፣

በክትትል ኦዲቱ ከተከለሱ ማስረጃዎች እና የኤጀንሲው ኃላፊዎች ከሠጡት መልስ ለመረዳት ተችሏል፡፡

## ወደ ማምረቻ፣ መሸጫና የገበያ ማዕከላት የሚገቡ ኢንተርፕራይዞችን በተመለከተ፤

43. ወደ ማምረቻ፣ መሸጫና የገበያ ማዕከላት የሚገቡ ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች የስራ መስኮች መስፈርት በጥቃቅንና አነስተኛ ልማት ኤጀንሲ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን መዘጋጀት አለበት፡፡ኢንተርፕራይዞች በመስፈርቱ መሰረት እየተመረጡ ወደየማዕከላቱ እንዲገቡ መደረግ አለበት፡፡

44. በቀድሞ ኦዲት ወቅት በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳዳር የሚገኙ 627 ሼዶች በህገ ወጥ መንገድ ለሶስተኛ ወገን የተከራዩ መሆኑ፤በተጨማሪም በናሙና በታዩ በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል፣ በኦሮሚያ ክልል እና በአዲስ አበባ ከተማ መስተዳደር በታዩ ማዕከላት የተዘጋጀውን መመልመያ መስፈርቶች ባልተከተለ መልኩ ወደ ማዕከላቱ የገቡ ግለሰቦችና ኢንተርፕራይዞች መኖራቸው፣ ወደ ማምረቻ ሕንፃ የሚገቡ ኢንተርፕራይዞች እንደ የሥራ ባህሪያቸው ሳይለዩ ወደ ህንጻው የገቡ በመሆኑ ኢንተርፕራይዞቹ በስራቸው ላይ ተጽኖ እንዳሳደረባቸውና በአንዳንድ ህንጻዎችም ላይ ጉዳት እንደደረሰባቸው በኦዲት ግኝቱ ተረጋግጦ ነበር፡

45. ወደ ማምረቻ፣ መሸጫና የገበያ ማዕከላት የሚገቡ ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች መምረጫ መስፈርት ተዘጋጅቶ በመስፈርቱ መሰረት ተግባራዊ ሊደረግ እና መስፈርቱ ያልተጣሰ ስለመሆኑም ኤጀንሲው ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመቀናጀት ክትትል የሚደረግበት አሠራር መዘርጋት እንዳለበት የማሻሻያ ሀሳብ ተሰጥቶ ነበር፡፡ ይህንንም ለመተግበር ኤጀንሲው የድርጊት መርሃ ግብር በማዘጋጀት ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ሊልክ ይገባል፡፡

46. በቀድሞው ኦዲት በተሰጠው የማሻሻያ ሀሳብ መሰረት የእርምት እርምጃ የሚወስድበትን ጊዜ የሚያመላክት የድርጊት መረሃ-ግብር ተዘጋጅቶ ለፌደራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ተልኳል፡፡

47. በክትትል ኦዲቱ ወቅት እንደታየው ፤

- የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎች ምርቶችን ለማምረት ከሚመለከተው አካል ተገቢውን የንግድ ምዝገባና ፈቃድ ያላቸው፤
- ካፒታላቸው ከብር ከ100,001 - 20 ሚሊዮን የሆነ የአነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎች፤
- ከፍተኛ የሰው ኃይል የሚጠቀሙ የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎች፤
- የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎቹ በብድር አመላለስ፣ በግብር አከፋፈል፣ ለሌሎች አርዓያ መሆን የቻሉ፤
- የተቋማቸዉን የሂሳብ መዝገብ አያያዝ ስርዓት በአግባቡ የዘረጉ፤ የተመሰከረላቸዉ፤ለውጭ ገበያ የሚሆኑ ምርቶችን የሚያመርቱ የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎች፤ በሥራቸው ብቃት ለአላቸው፣ ተወዳዳሪና ጥራት ያለው ምርት አምርተው ውጤት በማስመዝገብ ላይ የሚገኙ መሆን እንደሚኖርባቸው የሚገልጽ የማኑፋክቸሪንግ አምራች ኢንዱስትሪዎች

የመምረጫ መስፈርቶች እንዲዘጋጅ መደረጉ፣

- በሻሸመኔ ከተማ ወደ መካከለኛ ባለሀብትነት የተሸጋገሩ 7 ኢንተርፕራይዞች መኖራቸው ፣በሀዋሳ ከተማ አስተዳደር ቱርሚ፣ ሲዳና ኤልቶ ኢንተርፕራይዞች ወደ መካከለኛ ባለሀብትነት እንዲሸጋገሩ መደረጉ፣ ለኢንዱስትሪዎች ያልተላለፉ ማዕከላትን ኮርፖሬሽኑ አዲስ ባጠናው ዋጋ ተመን መሠረት እንዲስተናገዱ መደረጉ፣
- የሶማሌ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ፣የሀረሪ ህዝብ ክልላዊ መንግስት እና የድሬደዋ ከተማ አስተዳደር የ2010 የመጀመሪያ ዙር የድጋፍና ክትትል ሪፖርት ላይ በሶማሌ ክልል የኢንዱስትሪ ክላስተር ልማት ኮርፖሬሽን ድርጅታዊ መዋቅር አለመኖሩ፣የኢንዱስትሪ ክላስተር ልማት ኮርፖሬሽን ባለመኖሩ ነባር ሼዶችን ተረክቦ ለአነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎች አለመተላለፉ፣
- በ9 ክልሎችና በ2 ከተማ አስተዳደሮች የተለዩ ህንፃዎች ውስጥ የተገኙ ክፍት የማምረቻ ቦታዎች በእድገት ተኮር ዘርፎች ለተሰማሩ 150 የአነስተኛና መካከለኛ ኢንዱስትሪ አምራቾች በተገቢው ተለይተው ህጋዊነትን በተከተለ መልኩ መተላለፋቸውን ለማረጋገጥ በእቅድ የተያዘ ቢሆንም በዕቅድ ከተያዘው ውስጥ 77 የአነስተኛና መካከለኛ ኢንዱስትሪዎች ብቻ ክትትል መደረጉን ፣ በሱማሌ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት፣ የሀረሪ ህዝብ ክልላዊ መንግስት እና የድሬደዋ አስተዳደር የተለዩ ነባር ሼዶች ተረክቦና መሰረተ ልማትን አሟልቶ ለአነስተኛና መካከለኛ አምራች ኢንዱስትሪዎች ተላልፈው እንዲሰጡ አለመደረጉ፣
- በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል ከአጠቃላዩ የክላስተር ብሎኮች ለአነስተኛ እና ለመካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎች የተላለፉት 204 ብሎኮች በህንፃ እና በኢንዱስትሪዎች እድገት ደረጃ ተለይቶ መረጃው እንዲያዝ አለመደረጉ፣

በክትትል ኦዲቱ ከተከለሱ ማስረጃዎች እና የኤጀንሲው ኃላፊዎች ከሠጡት መልስ ለመረዳት ተችሏል፡፡

## የአነስተኛና ጥቃቅን ኢንተርፕራይዞች የፊትና የኋላ የገበያ ትስስርና ቁርኝት በተመለከተ፤

48. የማምረቻና የመሸጫ ማዕከላት ውስጥ የሚገቡ ኢንተርፕራይዞች የሚመጋገቡ፣ የፊትና የኋላ የገበያ ትስስርና ቁርኝት ሊፈጥር የሚችሉበት ሁኔታ መመቻቸት አለበት፡፡ በፌዴራሉም ሆነ በክልል የጥቃቅንና አነስተኛ ልማት ኤጀንሲዎች ይህ ትስስር መፈጠሩ መረጋገጥ አለበት፡፡

49. በቀድሞ ኦዲቱ ወቅት በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል፣ በኦሮሚያ ክልል እና በአዲስ አበባ ከተማ መስተዳደር በታዩ ወደ ማዕከላት በሚገቡ ኢንተርፕራይዞቹ መካከል የፊትና የኋላ የገበያ ትስስር አለመፈጠሩን፣

50. ወደ ማምረቻ ሕንፃ ወይም ሼድ የሚገቡ ኢንተርፕራይዞች የሚያመርቱትን ምርት የመሸጫና የማሳያ ቦታ እንደ ማይመቻችላቸው በኦዲት ግኝቱ ተረጋግጦ ነበር፡፡ ወደ ማምረቻና የመሸጫ ማዕከላት ውስጥ የሚገቡ ኢንተርፕራይዞች እርስ በርሳቸው የሚመጋገቡ፣ የፊትና የኋላ የገበያ ትስስርና ቁርኝት ሊፈጥሩ የሚችሉበት ሁኔታ ተመቻችቶላቸው ወደ መካከለኛ ኢንተርፕራይዝነት እንዲያድጉ ተገቢው ድጋፍ ሊደረግላቸው እንደሚገባ የማሻሻያ ሀሳብ ተሰጥቶ ነበር፡፡ ይህንንም ለመተግበር ኤጀንሲው የድርጊት መርሃ ግብር በማዘጋጀት ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ሊልክ ይገባል፡፡

51. በቀድሞው ኦዲት በተሰጠው የማሻሻያ ሀሳብ መሰረት የእርምት እርምጃ የሚወስድበትን ጊዜ የሚያመላክት የድርጊት መረሃ-ግብር ተዘጋጅቶ ለፌደራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ተልኳል፡፡

52. በክትትል ኦዲቱ ወቅት እንደታየው

- ለ300 ኢንዱስትሪዎች እና 60 ባለሞያዎች በአለምአቀፍ ግብይት ላይ ግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና ከCOMESA በተደረገ ድጋፍ ከኦሮሚያ ክልል 34 ከአዲስ አበባ 68 ከትግራይ 43 የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል 35 አማራ ክልል 45 በአጠቃላይ 225 ኢንዱስትሪዎች እና ከክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች ለተወጣጡ 40 የገበያ ባለሞያዎች የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና መሰጠቱ፤
- ከዲጂታል አፖርቹኒቲ ትረስት (DOT) መንግስታዊ ካልሆነ ድርጅት ጋር በመተባበር ከአዲስ አበባ ከተማ ለተወጣጡ 12 ኢንዱስትሪዎች በኤክስፖርት

ንግድ ስራ ልማት እና ኢ-ኮሜርስ ላይ በአዲስ አበባ ከተማ የልደታ ክፍለ ከተማ ኢንዱስትሪ ጽ/ቤት እና አራዳ ክፍለ ከተማ ኢንዱስትሪ ጽ/ቤት ጋር በመተባበር ለ85 ኢንዱስትሪዎች እና ለ62 የገበያ ባለሙያዎች ስልጠና መሰጠቱ፤አምራች ኢንዱስትሪዎች በኤክስፖርት ሂደት ውስጥ ያጋጠሟቸውን ችግር በዳሰሳ ጥናት በማጥናት እንዲለይ መደረጉ፤

- የአገር አቀፍ ኢግዚቪሽንና ባዛር (ኢትዮ ቻንበር፤ቦትስዋና፤ሱዳንና ኢናሚስ ኢንተርፕራይዝ በተዘጋጀው 43 ኢንዱስትሪዎች እንዲሳተፉ መደረጉ፤
- በ2010ዓ.ም. 640 ኢግዚብሽንና ባዛር በማዘጋጀት 25,600 ኢንዱስትሪዎች እንዲሳተፉ በማድረግ የብር 256.000.000 የገበያ ትስስር እንዲፈጠር ለማድረግ በእቅድ የተያዘ ቢሆንም 211 ኤግዚቪሽንና ባዛር በማጋጀት 7588 ኢንተርፕራይዞች እንዲሳተፉ በማድረግ የብር 60.622.553 የገበያ ትስስር የተፈጠረ ሲሆን አፈፃፀሙ በተዘጋጀ የኢግዚቪሽን ብዛት 32.9% በተሳታፊ ኢንተርፕራይዝ በዛት 29.6% በተፈጠረ የገበያ ትስስር የገንዘብ ብዛት 23.6% ሲሆን፤ አፈፃፀሙ በጣም ዝቅተኛ መሆኑ፣
- በ2010 በጀት አመት አዲስ 100 እና ነባር 395 ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎች የብር 204.160.559 እና 77.952.283 ኪሎ ግራም ናሙና እንዲያስተዋውቁና በቀጥታም ሆነ ከላኪዎች ጋር የገበያ ትስስር እንዲፈጠር እቅድ የተያዘ መሆኑንና አፈፃፀሙ 300 ነባር እና 206 አዲስ ኢንተርፕራይዝ ተጠቃሚ የተደረጉ ሲሆን 208.075.467 ዶላር ዋጋ ያላቸው 19.304.097.30 ኪሎግራም የተለያዩ የማኑፋክቸሪንግ ምርቶች ውጤቶች ወደ ውጭ ሀገር ለመላክ የተቻለ ቢሆንም አፈፃፀሙ በምርት ብዛት 25% ብቻ መሆኑ፣
- በየክልሎችና ዞኖች በከተሞች የሚገኙ የአነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎች በሌሎች ክልሎች ዞኖች እና ከተሞች ከሚገኙ ጋር እርስ በእርሳቸው የገበያ ትስስር እንዲፈጠር የሚያስችል አሰራሮችን በመዘርጋት አራቱን የግብይት ስርዓት ፍራንቻይዚንግ፤አውትግሮይንግ፤አውት ሶርሲንግና ሰብ ኮንትራክቲንግ እንዲጠቀሙ በማድረግ አፈፃፀሙን በአመት አንድ ጊዜ መከታተልና ግብረ መልስ የመስጠት ስራ በእቅድ የተያዘ ቢሆንም በአማራ፤ በትግራይ እና በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች የተሰራ ሲሆን በሌሎች ክልሎች ከተማ አስተዳደሮች ስራውን የሚተገብር አካል ባለመኖሩና ያለውም በቂ ግንዛቤ ስለሌላቸው ኢንዱስትሪዎቹን ተጠቃሚ ማድረግ አለመቻሉ፣

- ወደ የመሸጫ ሱቅ(ኢምፖሪየም)የገቡ ኢንድስትሪዎች 6 ወር ሞልቷቸው ምርታቸውን ያስወጡት ኢንዱስትሪዎች 22 መሆናቸው አፈፃፀሙ 23% መሆኑ፤
- የ2010 የገበያ ልማትና ኢንዱስትሪዎች ትስስር ዳይሬክተር ዓመታዊ አፈፃፀም ሪፖርት ላይ የ95 አነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎች ምርቶች የመሸጫ ሱቅ (ኢምፖሪየም) ውስጥ ለእይታ በሚመች ቦታና ሁኔታ በመደርደር የብር 4.016.706.75 የምርት ሽያጭ ለማከናወን ታቅዶ የ53 ኢንድስትሪዎች ምርት የብር 1.092.258.96 ሽያጭ የተከናወነ ሲሆን አፈፃፀሙ በሽያጭ 27% ብቻ መሆኑ፣

በክትትል ኦዲቱ ከተከለሱ ማስረጃዎች እና የኤጀንሲው ኃላፊዎች ከሠጡት መልስ ለመረዳት ተችሏል፤

## የማዕከል የቆይታ ጊዜ ጨርሰው ለሚወጡ ኢንተርፕራይዞች ስለሚደረግ ድጋፍ በተመለከተ፤

53. የማምረቻና መሸጫ ማዕከላት ውስጥ ተደራጅተው የገቡ ኢንተርፕራይዞች ከማዕከላቱ የመውጫ ጊዜ ከመድረሱ አስቀድሞ ሄደው የሚገቡበት በኢንዱስትሪ ዞኖች እንደ ሥራው ባህሪያቸው ለኢንተርፕራዞቹ አስቀድሞ ቦታ መዘጋጀት አለበት፡፡

54. በቀድሞ ኦዲት ወቅት በናሙና በታዩ በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል፣ በኦሮሚያ ክልል እና በአዲስ አበባ ከተማ መስተዳደር በታዩ የቆይታ ጊዜቸውን ጨርሰው የሚወጡ ኢንተርፕራይዞች ከተመረቁ በኃላ ምንም ዓይነት ድጋፍ እንደማይደረግላቸውና ግማሾቹም ከማዕከላቱ ያልወጡ መሆኑ በኦዲት ግኝቱ ተረጋግጦ ነበር፡፡

55. ከማዕከላቱ የመውጫ ጊዜ ከመድረሱ አስቀድሞ ወደመካከለኛ ኢንተፕራይዝነት ለሚሸጋገሩ ተቋማት በኢንዱስትሪ ዞኖች ውስጥም ሆነ በሌላ አመቺ በሆኑ ሥፍራዎች ለእያንዳንዱ ኢንተርፕራይዝ እንደ ሥራው ባህሪያቸው በመመሪያው መሰረት አስቀድሞ ቦታ ሊዘጋጅላቸው እና ተገቢው የፋይናንስ አቅርቦት የሚያገኙበት መንገድ ሊዘጋጅላቸው እንደሚገባ የማሻሻያ ሀሳብ ተሰጥቶ ነበር፡፡ይህንንም ለመተግበር ኤጀንሲው የድርጊት መርሃ ግብር በማዘጋጀት ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ሊልክ ይገባል፡፡

56. በቀድሞው ኦዲት በተሰጠው የማሻሻያ ሀሳብ መሰረት የእርምት እርምጃ የሚወስድበትን ጊዜ የሚያመላክት የድርጊት መረሃ-ግብር ተዘጋጅቶ ለፌደራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ተልኳል፡፡

57. በክትትል ኦዲቱ ወቅት እንደታየው

- ለአነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎች የድጋፍ ማዕቀፎች በማዘጋጀት በድጋፍ ማዕቀፍ መሰረት ለሚሸጋገሩ ኢንዱስትሪዎች ድጋፍና ክትትል መደረጉን በተመለከተ በኤጀንሲው አስር (10) የድጋፍ ማዕቀፎች ተዘጋጅተውና ጸድቀው ለክልሎች እንዲወርዱ መደረጉ፤ክልሎችም የወረደላቸውን መሰረት በማድረግ ከራሳቸው ነባራዊ ሁኔታ ጋር በማጣጣም የራሳቸውን ማዘጋጀታቸው፣
- በፌዴራል ደረጃ በተዘጋጁት የድጋፍ ማዕቀፎችና በኢንዱስትሪ ልማት ስትራቴጂ ላይ በ2011 በጀት ዓመት የመጀመሪያ ግማሽ ዓመት በሐዋሳ ከተማ ስልጠና መሰጠቱ፤
- አጠቃላይ ለአነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎች በሚሠጡ ድጋፎች ላይ ክትትል በማድረግ (በመስክ ጭምር)፣ በመድረክ በመገምገምና ግብረ-መልስ በመስጠት ስራውን ለመምራት ጥረት በመደረግ ላይ መሆኑ፣
- ሽግግርን በተመለከተ በ2008 በጀት ዓመት የካቲት ወር ላይ በአዲስ መልክ በተደራጀው ተቋም ተልዕኮ ውስጥ ሽግግሩ የሚደረገው ከአነስተኛ ማኑፋክቸሪንግ ወደ መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ሲሆን ኢንተርፕራይዞቹ ክፍተትን መሰረት ያደረገ ድጋፍ እንዲያገኙ በማመቻቸት እየተስፋፉ እንዲመጡ የሚደረግ መሆኑ፣

በክትትል ኦዲቱ ከተከለሱ ማስረጃዎች እና የኤጀንሲው ኃላፊዎች ከሠጡት መልስ ለመረዳት ተችሏል፡፡

## ለጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት በሚመለከታቸው አካላት መካከል ያለ ቅንጅታዊ አሰራርን በተመለከተ ፤

58. ለጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች የፋይናንስና ብድር አቅርቦት እና የማምረቻና የመሸጫ ማዕከላት ድጋፍ ላይ የአነስተኛ ፋይናንስ አቅራቢ ተቋማት፣ የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ኤጀንሲ ጽ/ቤት እና በየደረጃው ያሉ አመራሮች በቅንጅት ሊያቅዱና በዕቅዱ መሰረት ተግባራዊ መደረግ አለበት፡፡

59. በቀድሞ ኦዲት ወቅት  የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች እና ህዝቦች፣ በኦሮሚያ ክልሎች እና በአዲስ አበባ ከተማ መስተዳደር በናሙና ከታዮት የፋይናንስ ተቋማት እና ሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር ኤጀንሲው ያለው ቅንጅታዊ አሰራር ወጥነት ባለው መልኩ የማይከናወን መሆኑን፣ በተለይም ብድር የማስመለስ ሂደት ላይ ተጽዕኖ ማሳደሩን እና በክልሎችና በከተማ መስተዳድሮች የሚገኙ የአነስተኛና ጥቃቅን ኢንተርፕራይዞች ልማት የሚመለከታቸው ፈጻሚና ባለድርሻ አካላት የተቀናጀ የክትትልና የድጋፍ ሥርዓት የተዘረጋ ቢሆንም አተገባበር ላይ ወጥነት ባለው መልኩ አለመከናወኑን አለመዳበሩን በኦዲት ግኝቱ ተረጋግጦ ነበር፡፡

60. ለጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች የፋይናንስና ብድር አቅርቦት እና የማምረቻና የመሸጫ ማዕከላት ድጋፍ ላይ የአነስተኛ ፋይናንስ አቅራቢ ተቋማት፣ የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ኤጀንሲ ጽ/ቤት እና በየደረጃው ያሉ አመራሮች በቅንጅት ሊያቅዱና በዕቅዱም መሰረት ተግባራዊ ሊያደርጉ እንደሚገባ የማሻሻያ ሀሳብ ተሰጥቶ ነበር፡፡ይህንንም ለመተግበር ኤጀንሲው የድርጊት መርሃ ግብር በማዘጋጀት ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ሊልክ ይገባል፡፡ በቀድሞው ኦዲቱ በተሰጠው የማሻሻያ ሀሳብ መሰረት የእርምት እርምጃ የሚወስድበትን ጊዜ የሚያመላክት የድርጊት መረሃ-ግብር ተዘጋጅቶ ለፌደራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ተልኳል፡፡

61. በክትትል ኦዲቱ ወቅት እንደታየው፣

- የአነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎች ልማት ስትሪንግ ኮሚቴ በፌዴራል ደረጃ በምክትል ጠ/ሚኒስቴር ሰብሳቢነት እንዲመራ ሆኖ የተደራጀ ሲሆን የንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ሚንስትር እንዲሰበስብ ውክልና ተሰጥቶት እየተሰራበት መገኘቱ፣
- በክልል በዞንና በወረዳ ጭምር ስትሪንግ ኮሚቴው የተደራጀ መሆኑ ስትሪንግ ኮሚቴው በተቀመጠለት የውይይት ፕሮግራም መሰረት እየተሰበሰበ አለመሆኑ፣
- በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ልማት ለማስተባበርና ለመደገፍ መቋቋም ያለበት ስትሪንግ ኮሚቴ በየትኛውም እርከን ያልተቋቋመ መሆኑ፣
- በደቡብ በክልል ደረጃ 23 ተቋማትን ያካተተ በምክትል ርዕሰ መስተዳድሩ የሚመራ የማኑፋክቸሪንግ ድጋፍ ስቲሪንግ ኮሚቴ የተደራጀ ሲሆን የስቲሪንግ ኮሚቴው የጋራ ዕቅድ ተዘጋጅቶ ለሁሉም ሴክተር ተቋማት ለአስተያየት

የተሰጠ መሆኑ፤ ይሁንና የተዘጋጀውን ዕቅድ የጋራ በማድረግና በማፅደቅ ተፈራርመው ወደስራ ያልገቡ መሆኑ፣

- በጋምቤላ በክልል ደረጃ 8 አባላት ያሉት የስቲሪንግ ኮሚቴ የተቋቋመ መሆኑ፤ ይሁንና በስትሪንግ ኮሚቴው መካተት ያለባቸውን ተቋማት በአግባቡ በመለየትና የስትሪንግ ኮሚቴው አባል እንዲሆኑ እቅድ በማውጣትና የግንኙነት ጊዜ በማስቀመጥ የዘርፉን የልማት ስራዎችን እየገመገሙአለመሆኑ፤
- በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች በክልል ደረጃ የማኑፋክቸሪንግ ዘርፉን የሚደግፍና የሚከታተል ስቲሪንግ ኮሚቴ አሁን ባለበት ሁኔታ ተደራጅቶ ወደ ስራ ያልገባ መሆኑ፣
- በኦሮሚያ ክልል የአነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ልማት ለማስተባበርና ለመደገፍ መቋቋም ያለበት ስትሪንግ ኮሚቴ በየትኛውም እርከን ያልተቋቋ መሆኑ፣ የ2010 የዘጠኝ ወራት የጋራ እቅድ አፈፃፀም ላይ የቴክኒክ ኮሚቴ አባላት የጋራ የመስክ ጉብኝት ለማካሄድ በእቅድ የተያዘ ቢሆንም ለማከናወን አለመቻሉ፣

በክትትል ኦዲቱ ከተከለሱ ማስረጃዎች እና የኤጀንሲው ኃላፊዎች ከሠጡት መልስ ለመረዳት ተችሏል

# ክፍል ሦስት

## የመደምደሚያ ሀሳብ (Conclusion)

62. በቀድሞው የፌዴራል የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ኤጀንሲ የድጋፍ ማዕቀፍ አፈጻጸምን በተመለከተ በተሰራው ኦዲት ሪፖርት ላይ በተጠቀሱት የኦዲት ግኝቶች እና በተሰጡት የማሻሻያ ሀሳቦች ለአሁኑ የፌዴራል አነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎች ልማት ኤጀንሲን የሚመለከቱ ግኝቶች እና የኦዲት ማሻሻያ ሀሳቦች ላይ የተወሰደ እርምጃ መኖሩን ለማረጋገጥ በተከናወነው የክትትል ኦዲት የሚከተሉት መሻሻሎችና እንዲሁም እርምጃ ያልተወሰደባቸው ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡፡

እነርሱም፡-

### እርምጃ የተወሰደባቸውና መሻሻል የታየባቸው፤

- ለአዲስና ለነባር የአነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎች የብድር አቅርቦት በሚመለከት ከክልል ለተመለመሉ አስፈፃሚ አካላት የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና እንዲሰጥ መደረጉ፤
- የካፒታል ዕቃ ፋይናንስ ንግድ ስራ አክሲዎን ማህበር ለ1532 ወንድ እና ለ1035 ሴት በድምሩ ለ 2567 የኢንዱስትሪ ባለሀብቶች፤ሰራተኞች፤በካፒታል ዕቃ ፋይናንስ ድጋፍ ላይ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና መሰጠቱ፤
- የድጋፍ ማዕቀፍ አፈፃፀም ኦዲት ከየክልሉ ለተመለመሉ አስፈፃሚ አካላት የግንዛቤ ስልጠና እንዲሰጥ መደረጉ፤
- አዲስ ብድርና ቁጠባ ተቋምን በተመለከተ ስለ ወለድ አከፋፈል፤ ስለ አገልገሎት አሰጣጥ ስለ ኢንሹራንስ በቡድንና በማህበር ለተደራጁ በቴክኒክና ሞያ እና የአንድ ማዕከል አገልግሎት መስጫ ጣቢያ ላይ በባለሞያዎች ስልጠና መሰጠቱ፤
- በፌዴራል ባለስልጣን መ/ቤት ስር ከአለም ባንክ ከአውሮፓ ኢንቨስትመንት ባንክ በተገኘ ገንዘብ የአነስተኛ መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች ፋይናንስ ፕሮጀክት በቅርቡ ስራ የጀመረ ሲሆን በ2011 በጀት ዓመት የመጀመሪያ 6 ወር በተመረጡ ባንኮች ማይክሮ ፋይናንስ ተቋም አማካኝነት በልማት ባንክ በኩል የካፒታል እቃ ተጠቃሚ

ለሆኑ 121 ኢንዱስትሪዎች የብር 203.995.000 የስራ ማስኬጃ ብደር እንዲቀርብ መደረጉ፤

- ❖ አዲስ ብድርና ቁጠባ ተቋም አ.ማ ዋናው መስሪያ ቤት በዘርፍና በአደረጃጀት በመለየት የመክፈል አቅም ያላቸው የሌላቸው እንዲሁም የጠፉ ኢንተርፕራይዞች በወሰዱት የብድር መጠን ፤ ለምን ያህል ጊዜ እንደቆየ የሚያሳይ መረጃ በዝርዝር መያዙ፤
- ❖ ብድራቸውን መክፈል ላልቻሉት ሪእስኬጁል እና ሪፋይናንስ በማድረግ ከዚህ በተጨማሪ የእፎይታ ጊዜ በመስጠት ብድራቸውን እንዲከፍሉ መደረጉ፤
- ❖ በድሬደዋ ከተማ አስተዳደር ራሱን ችሎ የተቋቋመ ብድር ዋስትና ፈንድ ባይኖርም
- ❖ ከ ድሬ ብድርና ቁጠባ ተቋም ገቢ ማድረጋቸው፤፤ ከተማ አስተዳደሩም ለመደበው የብድር ዋስትና በጀት (ብር 4.000.000 ) ረቂቅ የአሰራር መመሪያ መዘጋጀቱ፤
- ❖ በሻሸመኔ ከተማ የብድር ዋስትና ፈንድ መመሪያ ተዘጋጅቶ እየተሰራበት መሆኑ፤ በማንዋሉ መሰረት በአፈፃፀም መመሪያው ላይም ስልጠና ለኢንተርፕራይዞች እና ለማእከል ባለሞያዎች እንዲሰጥ መደረጉ፤
- ❖ ከበጀታቸው ላይ 4.000.000 ለብድር ዋስትና በመመደብ ለድሬበቢዝነስ ፕላኑ መሰረት ቦታ ማዘጋጀታቸውን በክትትል ፎርማት ተዘጋጅቶ ክትትል መደረጉ፤
- ❖ የብድር ገንዘቡም የሚለቀቀው በየደረጃው ሲሆን በመጀመሪያ የስራ ማስኬጃ ይለቀቃል ፤በመቀጠልም የስራው እንቅስቃሴ አዋጭነት ታይቶ ቀሪው እንዲለቀቅ መደረጉ፤
- ❖ ብድር ለወሰዱ የአነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎች የቅርብ ክትትልና ድጋፍ ማድረግ የሚያስችል ስርዓት በመዘርጋት ተግባራዊ ማድረግን በተመለከተ ስራው የካፒታል እቃ ፋይናንስ ተቋም እና የብድር አቅራቢ ተቋማት በየደረጃው ካለው የዘርፍ መዋቅር ጋር በቅንጅት የሚሰራ በመሆኑ ከ2009 ጀምሮ በየሩብ አመቱ የፋይናንስ አቅርቦትን አስመልክቶ የሚመለከታቸው የክልልና የፌዴራል አስፈፃሚ ባለድርሻ አካላት እንዲገኙ በማድረግ ሪፖርት ቀርቦ ውይይት የሚደረግበት የክትትልና ድጋፍ አሰራር ተግባራዊ በመደረግ ላይ መሆኑ፤
- ❖ ብድር ከመሰጠቱ በፊት የሚቀርቡ ቢዝነስ ፕላን አዋጭ መሆኑ እንዲጠና መደረጉን በተመለከተ በካፒታል እቃ ፋናንስ እና በስራ ማስኬጃ ብድር አቅርቦት አዋጭ ቢዝነስ ፕላንና አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝም የአዋጭነት ጥናት ማቅረብን

የሚጠይቅ በመሆኑ ኢንተርፕራይዞች ብድር ለጠየቁት ተቋም እንዲያቀርቡ መደረጉ ፤

- በ2009 በጀት ዓመት ለልማት ባንክና ለካፒታል ዕቃ ፋይናንስ አቅራቢ ተቋምት 3403 ቢዝነስ ፕላን ቀርቦ 2622 የፀደቀ ሲሆን በ2010 በጀት አመት ደግሞ 1971 ቢዝነስ ፕላኖች ቀርበው 1585 ቢዝነስ ፕላኖች የጸደቁ መሆኑ፤
- በኢንዱስትሪዎች በኩል የሚቀርቡ ቢዝነስ ፕላኖች ክፍተት ያለባቸው በመሆኑ ይህንን ለሚደግፉ አስፈፃሚ አካላት በተሻለ ጥራት ያለው ቢዝነስ ፕላን እንዲቀርብ በፌዴራል ደረጃ የአስፈፃሚ አካላትን አቅም ለመገንባት  በቢዝነስ ፕላን አዘገጃጀት ላይ ስልጠና መሰጠቱ፤
- በ2010 በጀት ዓመት ለ400 ባለሞያዎች፤ በንግድ ስራ እቅድ አዘገጃጀት ላይ ስልጠና ለመስጠት ታቅዶ ለ795 (199% ስልጠና መሰጠቱ፤
- በ2009 በጀት አመት የትግራይ ክልል ለ416 ኢንዱስትሪዎችና ባለሀብቶችና ሰራተኞች በንግድ ዕቅድ አዘገጃጀት ላይ ስልጠና መሰጠቱ ፤በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች እና ህዝቦች ክልላዊ መንግሥት ክልልም በ2009 በጀት ዓመት በ416 እንዲሁም በ2010 በጀት ዓመት በ523 ቢዝነስ ፕላን ዝግጅት ድጋፍ መደረጉ፤
- አለም አቀፍ ደረጃውን የጠበቀ የክላስተር ማዕከላት ዲዛይን በሞዴልነት ለማባዛት ቀደም ሲል የማስተር ፕላኑና የአርክቴክቸራል ዲዛይን ስራውን በሠራው የምህንድስና አማካሪ ድርጅት ለሁሉም ክልሎች እና ከተማ አስተዳደሮች የሚሆን የNational Prototype Design በማሰራትና ክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች ኮርፖሬሽኖች Adapte አድርገው እንዲጠቀሙበት ዲዛይኖቹ እንዲደርሳቸው መደረጉ፤
- ክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች ለማምረቻ ክላስተሮች ግንባታ የሚውል መሬት በእስታንዳርዱ መሰረት እንዲዘጋጅ ማድረጋቸው፤
- በሀረሪ ክልል መሬት ዝግጅትን በተመለከተ  በክልል ደረጃ  መዘጋጀት  ከሚገባው ባለ 100 እና ባለ 250  ሄክታር ውስጥ  ባለ 50 ሄክታር መሬት መዘጋጀቱ፤
- በሻሸመኔ በከተማ አስተዳደሩ በኩል የሚመለከታቸው የኮንስትራክሽን ቢሮ ፤የከተማ ልማት ቢሮ ፤ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ በጋራ በመሆን ክትትልና ድጋፍ የሚያደርጉ መሆኑ፤

- ለነባር የማምረቻ ማዕከላት የመሠረተ ልማት ለማሟላት የመረጃ ችግሮች ቢኖሩም መረጃን በተገኘው አጋጣሚ በማሰባሰብ ከባለድርሻ ተቋማት ጋር የመሥራት ውስንነት ቢኖረውም እንዲቀጥል መደረጉ፤
- የአነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎች ዝርዝር መረጃ በአገር አቀፍ ደረጃ ወጥ በሆነ መልኩ ለመሰብሰብ እንዲቻል ቅፅና ማንዋል በኤጀንሲው ተዘጋጅቶ ለየክልሉ መላኩ፤
- ከክልል ለመጡ ኃላፊዎች እና ባለሞያዎች በመረጃ አሰባሰብ፣አያያዝና አደረጃጀት ላይ ስልጠና መሰጠቱ፤
- የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎች ምርቶችን ለማምረት ከሚመለከተው አካል ተገቢውን የንግድ ምዝገባና ፈቃድ ያላቸው፤
- ካፒታላቸው ከብር ከ100,001 - 20 ሚሊዮን የሆነ የአነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎች፣ከፍተኛ የሰው ኃይል የሚጠቀሙ የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎች፤
- የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎቹ በብድር አመላለስ፣ በግብር አከፋፈል፣ ለሌሎች አርዓያ መሆን የቻሉ፤
- የተቋማቸዉን የሂሳብ መዝገብ አያያዝ ስርዓት በአግባቡ የዘረጉ፤ የተመሰከረላቸዉ፣ ለውጭ ገበያ የሚሆኑ ምርቶችን የሚያመርቱ የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎች፤
- በሥራቸው ብቃት ለአላቸው፣ ተወዳዳሪና ጥራት ያለው ምርት አምርተው ውጤት በማስመዝገብ ላይ የሚገኙ መሆን እንደሚኖርባቸው የሚገልጽ የማኑፋክቸሪንግ አምራች ኢንዱስትሪዎች የመምረጫ መስፈርቶች እንዲዘጋጅ መደረጉ፤
- በሻሸመኔ ከተማ ወደ መካከለኛ ባለሀብትነት የተሸጋገሩ 7 ኢንተርፕራይዞች መኖራቸው፤
- በሀዋሳ ከተማ አስተዳደር ቱርሚ፤ሲዳና ኤልቶ ኢንተርፕራይዞች ወደ መካከለኛ ባለሀብትነት እንዲሸጋገሩ መደረጉ፤
- ለኢንዱስትሪዎች ያልተላለፉ ማዕከላትን ኮርፖሬሽኑ አዲስ ባጠናው ዋጋ ተመን መሠረት እንዲስተናገዱ መደረጉ፤
- በክትትል ኦዲቱ ወቅት ለ300 ኢንዱስትሪዎች እና 60 ባለሞያዎች በአለምአቀፍ ግብይት ላይ ግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና ከCOMESA በተደረገ ድጋፍ ከኦሮሚያ ክልል 34 ከአዲስ አበባ 68 ከትግራይ 43 የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል 35 አማራ ክልል 45 በአጠቃላይ 225 ኢንዱስትሪዎች እና ከክልሎችና

ከተማ አስተዳደሮች ለተወጣጡ 40 የገበያ ባለሞያዎች የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና መሰጠቱ፤

- ❖ ከዲጂታል አፖርቹኒቲ ትረስት (DOT) መንግስታዊ ካልሆነ ድርጅት ጋር በመተባበር ከአዲስ አበባ ከተማ ለተወጣጡ 12 ኢንዱስትሪዎች በኤክስፖርት ንግድ ስራ ልማት እና ኢ-ኮሜርስ ላይ በአዲስ አበባ ከተማ የልደታ ክፍለ ከተማ ኢንዱስትሪ ጽ/ቤት እና አራዳ ክፍለ ከተማ ኢንዱስትሪ ጽ/ቤት ጋር በመተባበር ለ85 ኢንዱስትሪዎች እና ለ62 የገበያ ባለሙያዎች ስልጠና መሰጠቱ ፤
- ❖ አምራች ኢንዱስትሪዎች በኤክስፖርት ሂደት ውስጥ ያጋጠማቸውን ችግር በዳሰሳ ጥናት በማጥናት እንዲለይ መደረጉ፤
- ❖ የአገር አቀፍ ኢግዚቢሽንና ባዛር (ኢትዮ ቻንበር፣ቦትስዋና፣ሱዳንና ኢናሚስ ኢንተርፕራይዝ በተዘጋጀው 43 ኢንዱስትሪዎች እንዲሳተፉ መደረጉ፤
- ❖ ለአነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎች የድጋፍ ማዕቀፎች በማዘጋጀት በድጋፍ ማዕቀፍ መሰረት ለሚሸጋገሩ ኢንዱስትሪዎች ድጋፍና ክትትል መደረጉን በተመለከተ በኤጀንሲው አስር(10) የድጋፍ ማዕቀፎች ተዘጋጅተውና ጸድቀው ለክልሎች እንዲወርዱ መደረጉ፤
- ❖ ክልሎችም የወረደላቸውን መሰረት በማድረግ ከራሳቸው ነባራዊ ሁኔታ ጋር በማጣጣም የራሳቸውን ማዘጋጀታቸው፤
- ❖ በፌዴራል ደረጃ በተዘጋጁት የድጋፍ ማዕቀፎችና በኢንዱስትሪ ልማት ስትራቴጂ ላይ በ2011 በጀት ዓመት የመጀመሪያ ግማሽ ዓመት በሐዋሳ ከተማ ስልጠና መሰጠቱ፤
- ❖ አጠቃላይ ለአነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎች በሚሠጡ ድጋፎች ላይ ክትትል በማድረግ (በመስክ ጭምር)፣ በመድረክ በመገምገምና ግብረ-መልስ በመስጠት ስራውን ለመምራት ጥረት በመደረግ ላይ መሆኑ፤
- ❖ ሽግግርን በተመለከተ በ2008 በጀት ዓመት የካቲት ወር ላይ በአዲስ መልክ በተደራጀው ተቋም ተልዕኮ ውስጥ ሽግግሩ የሚደረገው ከአነስተኛ ማኑፋክቸሪንግ ወደ መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ሲሆን ኢንተርፕራይዞቹ ክፍተትን መሰረት ያደረገ ድጋፍ እንዲያገኙ በማመቻቸት እየተስፋፉ እንዲመጡ የሚደረግ መሆኑ፤
- ❖ የአነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎች ልማት ስትሪንግ ኮሚቴ በፌዴራል ደረጃ በምክትል ጠ/ሚኒስቴር ሰብሳቢነት እንዲመራ ሆኖ የተደራጀ

ሲሆን የንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ሚንስትር እንዲሰበስብ ውክልና ተሰጥቶት እየተሰራበት መገኘቱ፤

❖ በክልል በዞንና በወረዳ ጭምር ስትሪንግ ኮሚቴው የተደራጀ መሆኑ

## እርምጃ ያልተወሰደባቸው እና መሻሻል ያልታየባቸው፤

- ለአስፈፃሚዎች በተፈጠረው ግንዛቤ ላይ ተመስርቶ በሁሉም ክልሎች በስፋት ወደ ኢንዱስትሪዎች ስለመውረዱ ክትትል በማድረግ ሪፖርት እንዲቀርብ የማይደረግ መሆኑ፤
- የሀዋሳ ከተማ የስራ እድል ፈጠራና ኢንተርፕራይዝ፤ መክፈል ያልቻሉና ውዝፍ ብድር ያለባቸውን ኢንተርፕራይዞች በዘርፍ፤ባለባቸው የብድር ውዝፍ እዳ እና ለምን ያህል ጊዜ እንደቆየ የሚያሳይ የተዘዋዋሪ ብድር መረጃ ያለ ሲሆን፤የመደበኛ ብድር መረጃው የሌለ መሆኑ፤
- በ2009 እና በ2010 በጀት ዓመት የካፒታል እቃ ፋይናንስ ተጠቃሚ ከሆኑት ውስጥ የስራ ማስኬጃ ብድር ያገኙትን ኢንተርፕራይዞች መረጃ ለብቻው ተለይቶ ያልተያዘ መሆኑ፤
- የኢንዱስትሪዎች የፋይናንስ ድጋፍ የሚሟላው በሁለት መንገድ ሲሆን በጥሬ ገንዘብ በሚቀርብ ብድር (የስራ ማስኬጃ) እና በአይነት የሚሰጥ የፋይናንስ ድጋፍ (የካፒታል እቃ) ነው በዚህም የካፒታል እቃ ሊዝና ፋይናንስ ዳይሬክተር የ2009 በጀት አመታዊ ዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት ላይ በበጀት አመቱ 5012 ማኑፍክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎች ለስራ ማስኬጃ 5.455.000.000.00 ብድር ለማመቻቸት እቅድ የተያዘ ቢሆንም ብሔራዊ ባንክ የሪፖርት መላኪያ ፎርማቱን ወደ አነስተኛና የብድርና ቁጠባ ተቋም ማውረድ ባለመቻሉ የተሰራጨው የብድር መጠን የማይታወቅ መሆኑ፤
- በኤጀንሲው በሚደረግ የድጋፍ ማዕቀፍ አፈፃፀም ኦዲት በቀረበው የመረጃ ማጠቃለያ ቅፅ መሰረት በተዘጋጀ አጭር ርፖርት ላይ አዲስ ኢንተርፕራይዝና ነባር አንቀሳቃሾች የስራ ማስኬጃ ብድርን በተመለከተ ስራው በዋነኝነት በክልል ኢንዱስትሪ ቢሮዎች በአበዳሪና በካፒታል ዕቃ ፋይናንስ ተቋማት በቅንጅት የሚሰራ ሲሆን ለአነስተኛ መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎች የስራ ማስኬጃ ብድር መስጠትን በተመለከተ በክልሎች ከቀረበ ሪፖርት በመነሳት በ2009 በጀት ዓመት የተሰጠ የስራ ማስኬጃ ብድር መረጃ ከክልሎች ሪፖርት ያልቀረበ መሆኑ፤

- የካፒታል እቃ ሊዝና ፋይናንስ ዳይሬክተር የ2009 በጀት አመታዊ ዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት ላይ በበጀት አመቱ ለአነስተኛና መካከለኛ ኢንዱስትሪዎች 7 ቢሊየን ብር ለማመቻቸት እቅድ ተይዞ 338.743.757.13 ብር የተሰራጨ ሲሆን አፈፃፀሙም 4.8% መሆኑ፤
- በ2010 በጀት አመት ለ8000 አነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎች የብር 6 ቢሊየን የስራ ማስኬጃ ብድር በአበዳሪ ተቋማት እንዲሰራጭ ክትትል ድጋፍ ለማድረግ ዕቅድ ተይዞ የ3 ክልሎች (ትግራይ፤ሱማሌ እና ድሬደዋ ) ብቻ ለ817 አነስተኛና ማካከለኛ ኢንዱስትሪዎች የሥራ ማስኬጃ ብድር ብር 158.143.568.07 የተሰራጨ ሲሆን፤(የብድር እቅዱን 10.2%) እና በእቅድ ከተያዙት ኢንዱሰትሪዎች ውስጥ ብድር ያገኙት (2.9%) ሲሆን ይህም ከአመታዊ እቅዱ ጋር ሲነፃፀር በጣም ዝቅተኛ መሆኑ፤
- የኢንተርፕራይዞች ልማት ዳይሬክተር የ2010 አመታዊ የአፈፃፀም ሪፖርት ላይ በበጀት አመቱ ለወጣቶች የተሰራጨው ብድር መጠን ኦሮሚያ፤አማራ፤ደቡብ፤ ድሬደዋ፤ጋምቤላ፤አዲስ አበባና ቤንሻንጉል ጉምዝ ክልል ውጭ ሌሎች ክልሎች መረጃውን ለይተው ባለመላካቸው አፈፃፀሙ 29 % መሆኑ፤
- የካፒታል ዕቃ ሊዝና ፋይናንስ የ2010 በጀት ዓመታዊ ዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት በፌዴራል ደረጃ ለአነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎች የስራ ማስኬጃ ብድር የሚያቀርቡ የፋይናንስ ተቋማት ተለይተው ባለመታወቃቸው በጋራ እቅድ አውጥቶ ለመንቀሳቀስ እንቅፋት መሆኑ፤
- በሻሸመኔ ከተማ የኦሮሚያ ብድርና የአነስተኛ ብድር አቅራቢ ተቋማት ለጥቃቅን አነስተኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዞች ተደራሽ ስለመሆናቸው የሚያሳይ መረጃ ቢጠየቁም ለአንድ ኢንተርፕራይዝ ብቻ ብድር ያመቻቹ መሆኑ፤
- የካፒታል ዕቃ ፋይናንስ አቅርቦት በተመለከተ ለአነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎች የማምረቻ መሳሪያውን ዋጋ 20 በመቶ እንዲቆጥቡ በማድረግ ቀሪውን የካፒታል ዕቃ ተቋሙ በመሸፈንና መሳሪያውን ገዝቶ በመስጠት ኢንዱስትሪዎቹ እስከ አምስት ዓመት በሚደርስ ጊዜ ክፍያውን የሚፈፅሙበት በአይነት የሚደረግ የፋይናንስ ድጋፍ ሲሆን በዚህም መሰረት በ2009 በጀት አመት ለ2.949 አነስተኛ መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎች የብር 7 ቢሊየን ማምረቻ መሳሪ እንዲቀርብ ድጋፍ ክትትል ለማድረግ ታቅዶ በበጀት አመቱ 1058

ኢንዱስትሪዎች (የእቅዱን 35.9%) የብር 371.835.094.10 ማምረቻ መሳሪያ (የዕቅዱን 5.3%) የቀረበ መሆኑ፣

- በ2010 በጀት አመት ለ8354 አነስተኛ መከከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎች የብር 8.354.000.000 ማምረቻ መሳሪያ ለማቅረብ ታቅዶ ለ154 አዲስና 779 ነባር በድምሩ ለ933 ኢንዱስትሪዎች (የእቅዱን 11.17%) እና የብር 720.008.035.16 ማምረቻ መሳሪያ (የእቅዱን 8.6%) የቀረበ መሆኑ አፈፃፀሙ ከእቅድ አኳያ ሲታይ በጣም ዝቅተኛ መሆኑ፣
- ቁጠባን በተመለከተ ይህንን ስራ በዋናነት የሚያከናውኑት ክልሎች ሲሆኑ በሰሩት የግንዛቤ ፈጠራ ስራ ለካፒታል እቃ ፋይናንስ ድጋፍ እንደ ቅድመ ሁኔታ የሚጠየቀው 20 በመቶ ቅድመ ቁጠባ እንዲቆጥቡ በማድረግ ሲሆን የስራ ማስኬጃ ብድር ለማግኘት የተቆጠበውን መረጃ የመሰብሰብ ስራ በኤጀንሲው አለመከናወኑ፣

- የኤጀንሲው የድጋፍ ማዕቀፍ አፈፃፀም ኦዲት በቀረበው ሪፖርት ከኤጀንሲው በተጨማሪ ክልል መስተዳድር ፣የከተማ አስተዳደሮች ፣ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ወዘተ የሚሳተፉበት የድርጊት መርሀ ግብር ያዘጋጀ ቢሆንም እስከ አሁን ድረስ የብድር ዋስትና ፈንድ በየክልሎች እንዲቋቋም አለመደረጉ፣
- የብድር ዋስትና ፈንድ በሁሉም ክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች መቋቋሙን በተመለከተ የብድር ዋስትና ፈንድ ለማቋቋም መጀመሪያ ኢንዱስትሪዎች ብድር ማግኘት የልቻሉት ዋስትና ማቅረብ ባለመቻላቸው ሁሉም ክልሎች እና ከተማ አስተዳደሮች የብድር ዋስትና ፈንድ የአሰራር መመሪ አዘጋጅተው ተግባራዊ እንዲያደርጉ ኤጀንሲው ባዘጋጀው የድርጊት መረሃ ግብር ላይ ቢቀመጥም የብድር ዋስትና ፈንድ ባለመቋቋሙ ምክንያት ክልሎች የአሰራር መመሪያ ያላዘጋጁ መሆኑ ፣
- በሻሸመኔ ፣ሀዋሳ የስራእድል ፈጠራና የምግብ ዋስትና ፅ/ቤት የብድር ዋስትና ፈንድ የአሰራር መመሪያ እንዲዘጋጅ ተደርጓል የተባለ ቢሆንም የአሰራር መመሪያ ሊቀርብ አለመቻሉ፣
- በሀዋሳ፣በሻሸመኔ ስለብድር ዋስትና ፈንድ አሰራር ላይ ስለፈንዱ (ብድሩ) አጠቃቀም ለቀበሌ አስተዳደር፣ለአንድ ማዕከል ባለሞያዎች እና ለብድርና ቁጠባ

ባለሞያዎች ስልጠና እና ግንዛቤ ማስጨበጫ ተሰጥቷል ቢባልም ነገር ግን መረጃው በማዕከል የማይገኝ መሆኑ፤

- በሀዋሳ ከተማ የኦሞ ማይክሮ ፋይናንስ ተቋም፤የሃዋሳ ከተማ የስራ እድል ፈጠራና የኢንተርፕራይዞች ብድር ከመሰጠቱ በፊት የሚቀርቡ ቢዝነስ ፕላኖች አዋጭ መሆኑ እንዲጠና ስለመደረጉ የሚያሳይ መረጃ አለመኖሩ፤
- የካፒታል እቃ ሊዝና ፋይናንስ ዳይሬክተር የ2009 በጀት አመታዊ ዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት ላይ የተሰራጨው ብድር ለታለመለት አላማ መዋሉን 4 ጊዜ ክትትል ለማድረግ የታቀደ ቢሆንም የብድር መረጃውን ማግኘት ባለመቻሉ የብድር ክትትል ስራ ያልተሰራ መሆኑ፤
- የድጋፍ ማዕቀፍ አፈፃፀም ኦዲት ለማድረግ በቀረበው የመረጃ ማጠቃለያ ቅፅ መሰረት የተዘጋጀ አጭር ርፖርት ላይ የብድር ተጠቃሚ የሆኑ የአነስተኛ መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎች ብድር ከወሰዱ በኋላ በተዘጋጀው የንግድ እቅድ መሰረት ለታለመለት አላማ ስለማዋላቸው የቀረበ ማስረጃ የሌለ መሆኑ፤
- በሻሸመኔ ከተማ የኦሮሚያ ብድርና ቁጠባ ተቋም ለሻሸመኔ ቅርንጫፍ ብድር ተጠቃሚ ኢንተርፕራይዞች በተዘጋጀው የንግድ እቅድ ዝግጅት መሰረት ለታለመለት አላማ ስለማዋላቸው ክትትል ስለመደረጉ የሚያሳይ ማስረጃ የሌለ መሆኑ፤
- ኦሞ ማይክሮ ፋይናንስ ተቋም አ.ማ የምስራቅ ቅ/ፅ/ቤት ተጠቃሚ ኢንተርፕራይዞች በተዘጋጀው የንግድ እቅድ ዝግጅት መሰረት ለታለመለት አላማ ስለማዋላቸው ክትትል ስለመደረጉ ማስረጃ አለመቅረቡ፤
- ለኦሞ ማይክሮ ፋይናንስ ተቋም ሀዋሳ ከተማ የንግድ ስራ እቅድ የአዋጭነት ጥናት የማይጠና መሆኑ ነገር ግን የቀረበውን ቢዝነስ ፕላን የመገምገም ስራ የሚሰራ መሆኑ ፤ኦሞ ማይክሮ ፋይናንስ ተቋም አ.ማ የምስራቅ ቅ/ፅ/ቤት ብድር ከመሰጠቱ በፊት የሚቀርበው ቢዝነስ ፕላን አዋጭ መሆኑ እንዲጠና ስለመደረጉ የሚያሳይ ማስረጃ የሌለ መሆኑ፤
- የመሰረተ ልማትና ክላስተር ዳይሬክተር የአፈፃፀም ሪፖርት መሰረት በነባርና በአዲስ መልክ ሊገነቡ በታሰቡ የክላስተር ማዕከላትና በክላስተር አስተዳደር ስራዎች አዳዲስ አሰራሮች ዙሪያ የአቅም ግንባታ ለ180 አመራሮችና ባለሞያዎች 2 ጊዜ የውይይት መድረክ በማዘጋጀት የጋራ ግንዛቤ እንዲፈጠር ለማድረግ አቅድ የተያዘ ቢሆንም ስራው አለመሰራቱ፤

- በአማራ 6188 ሄክታር ፤በትግራይ 3474 ሄክታር ፤በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች 3068 ሄክታር እና በአዲስ ሄክታር የተዘጋጀ ሲሆን የፕሮቶ ታይፕ ዲዛይንም በፌዴራል ደረጃ ተዘጋጅቶ ለክልሎች እንዲደርስ የተደረገ ቢሆንም ክልሎች የግንባታ በጀት መድበው ወደ ስራ ያልገቡ መሆኑ፤
- በአማራ ክልል በተለያዩ ከተሞች የመሬት ዝግጅት በማድረግ 6234.85 ሄክታር መሬት ቢዘጋጅም ካሳ ተከፍሎበት ከሶስተኛ ወገን ነጻ የተደረገ መሬት መጠን በድምሩ ሲታይ 82.1 ሄክታር ብቻ መሆኑ፤በትግራይ ክልል 3473.85 ሄክታር መሬት ለክላስተር ልማት ቢዘጋጅም ካሳ ተከፍሎ ከሶስተኛ ወገን ነፃ የሆነው 384.98 ሄክታር መሬት ብቻ መሆኑ፡፡
- የ2010 በጀት አመት የዝግጅት ምዕራፍ የአዲስ አበባ እና የኦሮሚያ የክልል የተደረገ የክትትልና ድጋፍ ሪፖርት እንደተመለከተው የምህንድስና የRTS ጥናቶች ተጨባጭ የመሬቱን ዳታ (መረጃ) ሳይወስዱ ዝም ብለው የአከባቢውን ህብረተሰብ በቃል ጠይቀው ባገኙት መረጃ መሰረት ተደርጎ በመሰራቱ ምክንያት በአንድ አከባቢ መሆን ያሌለባቸው ምርቶች በአንድ ቦታ እንዲመረቱ መደረጉ፤ ለኤክስፖርት ሊሆኑ የሚገባቸውን ምርቶችን ለማምረት አለመቻሉ፤
- ቡልቡላ ላይ የተሰራው ስትራክቸራል ዲዛይን የንፋስ አቅጣጫው የተሳሳተ መሆኑ፤ በተጨማሪም ፎቶ ብቻ ካልሆነ በስተቀር ተጨባጭ ነገሮችን የሚያሳይና ያገናዘበ አለመሆኑ፡
- ውኃ የሚወጣበትን ቦታ በድጋሚ በኦሮሚያ ውሃ ሥራዎች ኢንተርፕራይዝ እያስጠኑ መሆኑ፤በጋምቤላና ፤በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች ክልል በተደረገ ድጋፍና ክትትል ሪፖርት እንደተመለከተው፤ በጋምቤላ ከተማ ለኢንዱስትሪ ክላስተር ማዕከል ግንባታ 250 ሄክታር መዘጋጀት ሲኖርበት 100 ሄክታር ብቻ መዘጋጀቱ እንዲሁም በ13 ወረዳዎች እና በ1 ልዩ ወረዳ መዘጋጀት ያለበት 50 ሄክታር መሬት ያለመዘጋጀቱ፣ በሶማሌ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ፤ በሐረሪ ህዝቦች ክልላዊ መንግስት እና የድሬደዋ ከተማ አስተዳደር የ2010 መጀመሪያ ዙር የድጋፍና ክትትል ሪፖርት እንደተመለከተው በሶማሌ ክልል ለክላስተር ማዕከላት መዘጋጀት የሚገባው ባለ 50 ፤ባለ 100 እና ባለ 250 ሄክታር መሬት ያልተዘጋጀ መሆኑና ከ 3ኛ ወገን ነፃ አለመደረጉን፤ለማስጀምር ያክል እንኳን ከክልሉም ሆነ SDG በጀት አለመመደቡ፤

- በሞዴልነት የክላስተር ማዕከላት ፕላን ለሌሎች ክልሎችና ከተሞች አገልግሎት እንዲውሉ ከሚለሙ እና ከሚለዩ መሬቶች ጋር የማጣጣም ስራ እንዲሰራ ክትትል የማድረግ ስራ በእቅድ የተያዘ ቢሆንም ያልተሰራ መሆኑ፤
- በክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች የተዘጋጀውን ክላስተር ማዕከላት ልማት ፕላን በተመረጡ ከተሞች መተግበር እንዲችሉ ክትትልና ድጋፍ የማድረግ ስራ በእቅዱ መሰረት ያልተሰራ መሆኑ፡፡
- የምርት ማሳያና መሸጫ ስታንዳርድ ዲዛይን ለማዘጋጀት በተያዘው እቅድ ላይ ዋናው ስራ የሚካሄድበት በጀት ከአጋር የልማት ድርጅቶች የሚገኝ ቢሆንም የምህድስና አማካሪ ድርጅቶችን ፍላጎት ለማወቅ የተዘጋጀውን የጨረታ ሰነድ እንዲደርሳቸው በኤጀንሲው በኩል ተግባራዊ ማድረግ አለመቻሉ፣
- በክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች በአዲስ መልክ በተዘጋጀው የክላስተር ማዕከላት ፕላን መሰረት ትኩረት በተሰጠባቸው ዘርፎች ለማምረቻነት የሚውሉ 106 ህንፃዎችን በስታንዳርድ ዲዛይን እንዲገነቡ ድጋፍ ለማድረግ እቅድ የተያዘ ቢሆንም ስራው ያልተሰራ መሆኑ ፤
- በማዕከላት እንዲሁም በኢንዱስትሪ ፓሮኮች ልማት ኮርፖሬሽን አደረጃጀት መጠናቀቅ ባለመቻሉ ነባር የክላስተር ማዕከላት ተረክቦ ተገቢውን መሰረተ ልማት በመሟላት ለኢንዱስትሪያሊስቶች ማሸጋገር ያልተቻለ መሆኑ፤በክልሎችና ከተማ አስተዳደሮችለማምረቻና ለመሸጫ ታስበው የተገነቡ ህንፃዎች በተላከላቸው የመረጃ ማሰባሰቢያ ፎርማት መሰረት የተሰበሰበው መረጃ 968 ህንፃዎች ሲሆኑ ከነዚህ ውስጥ 278 ህንፃዎች መሰረተ ልማት ያልተሟላላቸውና ለአነስተኛና መካከለኛ ኢንዱስትሪዎች አገልግሎት የማይሰጡ መሆናቸው፤
- ታዳጊ መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎች ማዕከላት የገቡ ኢንዱስትሪዎች መረጃ በማደራጀት ረገድ በነባር ማምረቻ ማዕከላት የክልሎች ወጥ የሆነ የአሰራር የባለቤትነት ችግር በመኖሩ መረጃው በአግባቡ ማደራጀት አለመቻሉ፤
- የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቢሮ የካ ፤ኮልፌ እና አቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተሞች በራሳቸው ቅፅ የሚጠቀሙ መሆኑን ለማረጋገጥ መቻሉ፤
- በጋንቤላ ክልል የአነስተኛ እና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎች ቆጠራ አለመደረጉ እና ከስራ እድል ፈጠራና ምግብ ዋስት ኤጀንሲ ወደ አነስተኛ እና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎች ልማት ኤጀንሲ አለመተላለፋቸው፣

- ክልሎች የላኩት መረጃ በሚፈለገው ደረጃ ጥራቱን ያልጠበቀና ያልተሟላ በመሆኑ በኦሮሚያ፤ በትግራይ፤በደቡብና ፤በአማራ ፤በሀረሪ ፤በአዲስ አበባ እንዲሁም በድሬደዋ ከተማ አስተዳደር የ2010 በጀት ዓመት የዝግጅት ምዕራፍ የድጋፍ ክትትል ስራ የተጠቃለለ ሪፖርት ላይ ዝርዝር የኢንተርፕራይዞች መረጃ መሰብሰብያ ቅፅን በተሟላ ሁኔታ እየተጠቀሙበት እንዳልሆነ የታየ ቢሆንም በተለያዩ ቅፆች መረጃዎችን ለማሰባሰብ ጥረት እየተደረገ ቢሆንም በተዘጋጀው ወጥነት ባለው የመረጃ ማሰባሰቢያ ፎርማት መሰረት የማይሰበሰብ መሆኑ፤
- በአፋርና በቤንሻንጉል ጉምዝ ክልል ከጥቅምት 6-13 /2010 በተደረገ ክትትልና ድጋፍ በክልሉ የሚገኙ አነስተኛ እና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎች የመለየት ስራ በአሶሳ ከተማ ብቻ ያሉት እንደተለዩና በሌሎች ዞኖች የሚገኙት ያልተለዩ መሆኑ፤ የሶማሌ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ፤የሀረሪ ህዝብ ክልላዊ መንግስት እና የድሬደዋ ከተማ አስተዳደር የ2010 የመጀመሪያ ዙር የድጋፍና ክትትል ሪፖርት ላይ በሶማሌ ክልል የኢንዱስትሪ ክላስተር ልማት ኮርፖሬሽን ድርጅታዊ መዋቅር አለመኖሩ፤
- የኢንዱስትሪ ክላስተር ልማት ኮርፖሬሽን ባለመኖሩ ነባር ሼዶችን ተረክቦ ለአነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎች አለመተላለፉ፤
- በ2009 የመሰረተ ልማትና ክላስተር ዳይሬክተር የአፈፃፀም ሪፖርት ላይ በ9 ክልሎችና በ2 ከተማ አስተዳደሮች የተለዩ ህንፃዎች ውስጥ የተገኙ ክፍት የማምረቻ ቦታዎች በእድገት ተኮር ዘርፎች ለተሰማሩ 150 የአነስተኛ መካከለኛ ኢንዱስትሪ አምራቾች በተገቢው ተለይተው ህጋዊነትን በተከተለ መልኩ መተላለፋቸውን ለማረጋገጥ በእቅድ የተያዘ ቢሆንም በዕቅድ ከተያዘው ውስጥ 77 የአነስተኛ መካከለኛ ኢንዱስትሪዎች ብቻ ክትትል መደረጉ፤
- በሱማሌ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ፤ የሀረሪ ህዝብ ክልላዊ መንግስት እና የድሬደዋ አስተዳደር የተለዩ ነባር ሼዶች ተረክቦና መሰረተ ልማትን አሟልቶ ለአነስተኛና መካከለኛ አምራች ኢንዱስትሪዎች ተላልፈው እንዲሰጡ አለመደረጉ፤
- በደቡብ ክልል ከአጠቃላዩ የክላስተር ብሎኮች ለአነስተኛ እና ለመካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎች የተላለፉት 204 ብሎኮች በህንፃ እና በኢንዱስትሪዎች እድገት ደረጃ ተለይቶ መረጃው እንዲያዝ አለመደረጉ፤
- በ2010 ዓ.ም. 640 ኢግዚብሽንና ባዛር በማዘጋጀት 25600 ኢንዱስትሪዎች እንዲሳተፉ በማድረግ የብር 256.000.000 የገበያ ትስስር እንዲፈጠር ለማድረግ

በእቅድ የተያዘ ቢሆንም 211 ኤግዚቪሽንና ባዛር በማጋጀት 7588 ኢንተርፕራይዞች እንዲሳተፉ በማድረግ የብር 60.622.553 የገበያ ትስስር የተፈጠረ ሲሆን አፈፃፀሙ በተዘጋጀ የኢግዚቪሽን ብዛት 32.9% በተሳታፊ ኢንተርፕራይዝ በዛት 29.6% በተፈጠረ የገበያ ትስስር የገንዘብ ብዛት 23.6% ሲሆን፤ አፈፃፀሙ በጣም ዝቅተኛ መሆኑ፤

- በ2010 በጀት አመት አዲስ 100 እና ነባር 395 ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎች የብር 204.160.559 እና 77.952.283 ኪሎ ግራም ናሙና እንዲያስተዋውቁና በቀጥታም ሆነ ከላኪዎች ጋር የገበያ ትስስር እንዲፈጠር እቅድ የተያዘ መሆኑንና አፈፃፀሙ 300 ነባር እና 206 አዲስ ኢንተርፕራይዝ ተጠቃሚ የተደረጉ ሲሆን 208.075.467 ዶላር ዋጋ ያላቸው 19.304.097.30 ኪሎግራም የተለያዩ የማኑፋክቸሪንግ ምርቶች ውጤቶች ወደ ውጭ ሀገር ለመላክ የተቻለ ቢሆንም አፈፃፀሙ በምርት ብዛት 25% ብቻ መሆኑ፤
- በየክልሎችና ዞኖች በከተሞች የሚገኙ የአነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎች በሌሎች ክልሎች ዞኖች እና ከተሞች ከሚገኙ ጋር እርስ በእርሳቸው የገበያ ትስስር እንዲፈጠር የሚያስችል አሰራሮችን በመዘርጋት አራቱን የግብይት ስርዓት ፍራንቻይዚንግ፣አውትግሮይንግ፣አውት ሶርሲንግና ሰብ ኮንትራክቲንግ እንዲጠቀሙ በማድረግ አፈፃፀሙን በአመት አንድ ጊዜ መከታተልና ግብረ መልስ የመስጠት ስራ በእቅድ የተያዘ ቢሆንም በአማራ፤ በትግራይ እና በደቡብ ክልል የተሰራ ሲሆን በሌሎች ክልሎች ከተማ አስተዳደሮች ስራውን የሚተገብር አካል ባለመኖሩና ያለውም በቂ ግንዛቤ ስለሌላቸው ኢንዱስትሪዎቹን ተጠቃሚ ማድረግ አለመቻሉ፤
- ወደ ኢምፐሪዩም የገቡ 95 ኢንዱስትሪዎች 6 ወር ሞልቷቸው ምርታቸውን ያስወጡት ኢንዱስትሪዎች 22 መሆናቸው አፈፃፀሙ 23% መሆኑ፤
- የ95 አነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎች ምርቶች በኢምፐሪየም ውስጥ ለእይታ በሚመች ቦታና ሁኔታ በመደርደር የብር 4.016.706.75 የምርት ሽያጭ ለማከናወን ታቅዶ የ53 ኢንዱስትሪዎች ምርት የብር 1.092.258.96 ሽያጭ የተከናወነ ሲሆን አፈፃፀሙ በሽያጭ 27% ብቻ መሆኑ፤
- ስትሪንግ ኮሚቴው በተቀመጠለት የውይይት ፕሮግራም መሰረት እየተሰበሰበ አለመሆኑ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ

ኢንዱስትሪ ልማት ለማስተባበርና ለመደገፍ መቋቋም ያለበት ስትሪንግ ኮሚቴ በየትኛውም እርከን ያልተቋቋመ መሆኑ፤

- በደቡብ በክልል ደረጃ 23 ተቋማትን ያካተተ በም/ርዕሰ መስተዳድሩ የሚመራ የማኑፋክቸሪንግ ድጋፍ ስቲሪንግ ኮሚቴ የተደራጀ ሲሆን የስቲሪንግ ኮሚቴው የጋራ ዕቅድ ተዘጋጅቶ ለሁሉም ሴክተር ተቋማት ለአስተያየት ተሰጥቷል፡፡ ይሁንና የተዘጋጀውን ዕቅድ የጋራ በማድረግና በማፅደቅ ተፈራርመው ወደስራ ያልገቡ መሆኑ፤
- በጋንቤላ በክልል ደረጃ 8 አባላት ያሉት የስቲሪንግ ኮሚቴ የተቋቋመ ቢሆንም በስትሪንግ ኮሚቴው መካተት ያለባቸውን ተቋማት በአግባቡ በመለየትና የስትሪንግ ኮሚቴው አባል እንዲሆኑ እቅድ በማውጣትና የግንኙነት ጊዜ በማስቀመጥ የዘርፉን የልማት ስራዎችን እየገመገሙአለመሆኑ፤
- በደቡብ ክልል በክልል ደረጃ የማኑፋክቸሪንግ ዘርፉን የሚደግፍና የሚከታተል ስቲሪንግ ኮሚቴ አሁን ባለበት ሁኔታ ተደራጅቶ ወደ ስራ ያልገባ መሆኑ፤
- በኦሮሚያ ክልል የአነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ልማት ለማስተባበርና ለመደገፍ መቋቋም ያለበት ስትሪንግ ኮሚቴ በየትኛውም እርከን ያልተቋቋ መሆኑ፤
- የ2010 የዘጠኝ ወራት የጋራ እቅድ አፈፃፀም ላይ የቴክኒክ ኮሚቴ አባላት የጋራ የመስክ ጉብኝት ለማካሄድ በእቅድ የተያዘ ቢሆንም ለማከናወን አለመቻሉ፣

ታውቋል፡፡

# ክፍል አራት

## የማሻሻያ ሀሳቦች (Recommendation)

63. ከላይ በክፍል ሁለት ላይ የተጠቀሱ ነባራዊ ሁኔታዎችን መሠረት በማድረግ የተደረሰባቸው መደምደሚያዎች በክፍል ሦስት ላይ ተጠቅሰዋል፡፡ በመሆኑም በመጀመሪያው ኦዲት ወቅት በተገኙ ግኝቶች ላይ የተሰጡት የማሻሻያ ሀሳቦች የተወሰኑት የእርምት እርምጃ የተወሰደባቸውና ማሻሻል የታየባቸው ሁኔታዎች በመኖራቸው ተጠናክሮ መቀጠል አለባቸው፡፡

64. ነገር ግን ከዚህ በፊት በተሰጠው የማሻሻያ ሀሳብ መሠረት ያልተስተካከሉና የእርምጃ ባልተወሰደባቸው የኦዲት ግኝቶች ላይ ከዚህ በፊት በተሰጠው የማሻሻያ ሀሳብ መሰረት ቀደም ሲል በተዘጋጀው የድርጊት መርሃ ግብር መሰረት አስፈላጊውን ክትትል በማድረግ የእርምት እርምጃ ሊወሰድ ይገባል፡፡

በመጨረሻም በክትትል ኦዲት ወቅት ስለተደረገልን የሥራ ትብብር እናመሰግናለን፡፡